COVERINGCRSV.ORG

# በግጭት ወቅት ስለ ወሲባዊ ጥቃት መዘገብ

ይህ መመሪያ በእንግሊዘኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽኛ፣ ስዋሂሊኛ እና አረብኛም ይገኛል።

© Dart Centre Europe | ሥሪት 1.0

# ይዘቶች

## ስለ እና ለምን

#1. ለዚህ በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቻለሁ?

#2. ይህንን ሰው በዚህ ጊዜ እና በዚህ ቦታ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለብን?

#3. ቃለመጠይቅ የማደርግላቸው ሰዎች በመሳተፋቸው ሊደርስባቸው የሚችል መዘዝ ሙሉ በሙሉ ተረድተዋልን?

#4. ተጎጂዎች በራሳቸው መንገድ እና በራሳቸው ጊዜ እንዲናገሩ ፍቀድላቸው

#5. አስቃቂነት በትውስታና እና የደህንነት ስሜት ላይ ያለው የማያቋርጥ ተጽእኖ ይረዱ

#6. የእራስዎ ስሜታዊ ደህንነት እንዴት የዚሁ አካል እንደሆነ ይረዱ

#7. ያስታውሱ፤ ጾታዊ ጥቃት መቼም ቢሆን የታሪኩ ብቸኛ ገጽታ አይደለም።

#8. ምስሎቹ አይጠፉም፤ በእይታ ምርጫዎች ይጠንቀቁ

© Dart Centre Europe

# ስለ

**የተወሰኑ የጋዜጠኛነት ተግዳሮቶች በግጭት ወቅት የተከሰቱ ወሲባዊ ጥቃቶችን ከመዘገብ በላይ ኃላፊነትን ተሸክመዋል። በጦርነት ወወቅት አሰገድዶ መድፈር ጥቅም ላይ ሲውል፣ በግለሰቦች እና በማህበረሰቦች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው።**

ኃላፊነት የሚሰማው ጋዜጠኛነት ሰዎች ሊገልፁት በቂ ቃላት ላጡት እና ለተቸገሩበት ወንጀል ትኩረት እና አንጻር ያበጅለታል። ግድየለሽነት የተሞላበት ጋዜጠኛነት በተቃራኒው፣ ተጎጂዎችን ለተጨማሪ አደጋ በማጋለጥ ጭንቀት እና ውጥረት ይጨምርባቸዋል። ይህ መመሪያ የተጻፈው በተደጋጋሚ በሲአርኤሺ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በሚሰሩ ጋዜጠኞች እና ፊልም ሰሪዎች ነው። መነሻውም እንደ ጋዜጠኛነት ተቋም ምርጥ ልምዶችን  ለማጋራት እና የበለጠ ለመበየን በመፈለግ ነው። ግቡም የበለጠ ትክክለኛ እና የተሻለ ግንዛቤ የታከለበት ዘገባ ፣ ታሪካቸውን የሚናገሩ ግለሰቦች ከደረሰባቸው ጥቃት በላይ የሚደርሰባቸውን ጉዳት በመቀነስ ማቅረብ እንዲቻል ለማድረግ ነው።

# ይህ ለምን?

**ይህ መመሪያ መነሻውን ያደረገው በግጭት በተጎዱ አገራት ከወሲባዊ ጥቃት እና ከሰቃይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ዘገባዎችን በመሰራት የካበተ ልምድ ያላቸው ጋዜጠኞች እና ፊልም ሰሪዎች ጋር በተደረገ ተደጋጋሚ ውይይት ነው።**

በዚህ ስራ ላይ የተሳተፉ በአጠቃላይ በጎ አስተዋጽኦ ለማበርከት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ነገር ግን ሁላችንም አንድ ቦታ ላይ ቆም ብለን ታሪካቸውን ለመንገር የምንፈልጋቸው ሰዎች ላይ በሚኖረን ተራክቦ ተጨማሪ ጉዳት አድርሰን ይሆን ስንል ጠይቀናል።

በግጭት ውስጥ የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸውን ግለሰቦች ቃለ መጠየቅ ለማድረግ ቀዳሚዎቹ የመገናኛ ብዙኀን ባልደረቦች ቢሆኑም ስልጠናና ድጋፍ የሚያገኙት ግን አልፎ አልፎ ነው።

ይኹን እንጂ ስልጠናና እና ድጋፍ ለማግኘት ግን ፍላጎት አለ። ይህ መመሪያ፤ በሲአርኤሰቪ ላይ ለመሰራት ፍላጎት ያለው ጋዜጠኛም ሆነ የፊልም ባለሙያ  ሊረዳው በሚችል፣ ሰምንት ቁልፍ የክህሎት ክፍሎች መድቦታል። እነዚህ ሰምንት ክፍሎች የተቀረፁት በጥልቀት እንዲነበቡ እንዲሁም በቀላሉ ለመከለስ እና ለባልደረባ ማጋራት እንዲቻል ተደርገው ነው። በተጨማሪም ተግባራዊ እንዲሆኑ እና መሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ታስቧል።

ይህ ለመገናኛ ብዙኀን ባልደረቦች በጋዜጠኞች የተዘጋጀው መመሪያ፣ ተከታታይ እና ሰፊ ከሆነ ውይይት በኋላ የተጻፈ ነው።

ይህንን መመሪያ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የሲአርኤሰቪ ተጠቂዎችን (የተወሰኑት አሁን የመብት አቀንቃኞች እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ባለሙያዎች ናቸው) ፣ የሰሜት ቀውሰን የሚያክሙ ባለሙያዎች፣ የማህበረሰብ ሰራተኞች እና ጠበቆችን እንዲሁም የፎቶግራፍ ባለሙያዎች፣ ፊልም ባለሙያዎች እና ከፍተኛ አዘጋጆችን አማክረናል።

ይህ ጉዳይ ወሰብሰብ ያለ ነው። ይህ መመሪያ አንድ የመገናኛ ብዙኀን ባልደረባ የሚገጥሙዋቸውን ተግዳሮቶች በሙሉ አይዳሰሰም፤ እንዲሁም እኛ ባቀረብናቸው ሁሉም ምክረ ሃሳቦች እንደማይሰማሙም ግልጽ ነው።

ይኹን እንጂ ሁለት እውነቶችን ለማስታረቅ በብርቱ ታግለናል። ቀዳሚው እነዚህ ጥቃቶች እንሰካልተሰነዱ ድረሰ የሚቆሙበት አንዳችም መንገድ የለም። ሁለተኛው ደግሞ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰበት እያንዳንዱ ግለሰብ ታሪኩ የግሉ ነው፤ የእኛ አይደለም።

# ከዚህ በኋላስ?

ይህንን መመሪያ ያዘጋጀነው ውይይትን እና ግንዛቤን ለመፍጠር በማሰብ ነው። እንድናጋራው የተዘጋጀ ነው። እባክዎ ይህንን መመሪያ በማንበብ ለሚጠቀም ሁሉ ያሰራጩ።

የእርሰዎን ግብረ መልስ እንጠብቃለን እንዲሁም ወደፊት በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ዝግጁ ነው።

ስለ ዳርት ማዕከል ስራዎች የበለጠ ለማወቅ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን የኢሜል ዝርዝሩ ላይ **እዚህ** ይመዝገቡ።

# አስተዋጽኦ እና ምስጋናዎች

ይህ መረጃ”፡ አሰቃቂ እና ግጭትን በሚዘግቡ ጋዜጠኞች እና የፊልም ሰሪዎች ትብብር የተቋቋመ **ዳርት ሴንተር አውሮጳ** በተሰኘው ጥምረት የተዘጋጀ ነው። ስለዚህየመጀመርያው ምስጋና ላለፉት አመታት በማዕከሉ ውስጥ ለተደረጉ ውይይቶች አስተዋጽኦ ላደረጉ ሁሉ መቅረብ አለበት። ዋናው የማደራጀት እና የጽሑፍ ቡድን **ጋቪን ሪዝ**፣ **ሳሚራ ሻክል**፣ **እስቲፈን ጁክስ**፣ **ጁሊያና ሩህፉስ**፣ **ሌዝሊ ቶማስ** እና **ክርስቲና ላምብ** ያቀፈ ነበር።

በቀጥታ ምክክራችን ላይ ለተሳተፉት ሁሉ እናመሰግናለን።

DART CENTRE EUROPE

ይህን ፕሮጀክት መፈጸም የተቻለው የዩናይትድ ኪንግደም በየውጭ፣ የኮመንዌልዝ እና የልማት ጽህፈት ቤት፣ በግጭት ውስጥ የሚደረጉ የፆታ ጥቃትን የመከላከል ተቋም ባበረከተው የገንዘብ ድጋፍ ነው።

ዳርት ማዕከል በአውሮፓ
የማሕበሩ የምዝገባ ቁጥር በኢንግላንድ እና በዌልስ፤ 1172731
እባክዎ ያግኙን። አስተያየትዎን መስማት እንፈልጋለን **covering.crsv@dartcentre.org**

እባክዎን በግራጫ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

# #1.

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

# ለዚህ በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቻለሁ?

# #1.

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

## ለዚህ በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቻለሁ?

በግጭት ቀጠና ውስጥ ስለ ወሲባዊ ጥቃት ከመገናኛ ብዙኃን ጋር መነጋገር ለማንኛውም የጥቃቱ ሰለባ የሆነች ሰው ከፍተኛ አደጋ አለው። እነዚህ መመሪያዎች አደጋው ምን እንደሆነ የተሻለ ግንዛቤ ይሰጡዎታል።

**አንድ ጋዜጠኛ ከሚወስዳቸው በጣም ፈታኝ ሥራዎች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) መዘገብ ቅድሚያ ይይዛል - ደግሞ በጥንቃቄ ማሰብን የሚጠይቅ ነው ። ሥራ ከመጀመርዎ በፊት የሚከተሉትን ገፅታዎች መመርመርዎን ያረጋግጡ።**

- **ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ምን እንደሆነ እና አስገድዶ መድፈር እንዲሁም በሌላ መልክ የሚደርሱ ወሲባዊ ጥቃቶች በግለሰቦች እና በማህበረሰቦቻቸው የሚያሳድሩት ተጽዕኖ**
- **አስቃቂነቱ በሚያገናዝብ መልኩ እና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ተጎጂዎችን እንዴት ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደሚቻል**
- **በአካባቢው ያለው ፖለቲካዊ ስልጣን እና አጠቃላይ የደህንነት ሥዕል፣ የሥርዓተ ፆታ ሁኔታዎች እና ስለ ፆታዊ ጥቃትን ያለ ባህላዊ አመለካከቶች**
- **ሊያቀርቡት የሚፈልጓቸው ምስላዊ ምርጫዎች። የሰዎችን ፎቶግራፍ ያነሳሉ ወይም ቪድዮ ይቀርጻሉ? እንዴት እና የት ያደርጉታል? ስም-አልባ ይሆናሉ?**
- **የራስዎ የስነ-ልቦና ዝግጁነት ደረጃ እና ለምን አስፈላጊ እንደሆነ**

ይህንን መመሪያ የግጭት **ጊዜ ወሲባዊ ጥቃት ዘገባ ብለን** ጠርተነዋል። ነገር ግን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የሚያመለክተውን መደበኛ የእንግሊዝኛ ምህፃረ ቃል CRSV እንጠቀማለን።

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV)፣ ለምሳሌ፤ አስገድዶ መድፈር፣ ተገድዶ አዳሪነት፣ በአስገዳጅ ጋብቻ ውስጥ የሚደረግ ማምከን፣ እና ከግጭቶች ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ሌሎች ተመሳሳይ ወንጀሎች ያመለክታል። እነዚህ ወንጀሎች ብዙውን ጊዜ ወታደራዊ ወይም የፖለቲካ ግቦችን ለማሳካት ተብሎ የሚፈፀሙ ናቸው። ስለሆነም በሕጋዊ የዘር ማጥፋት እና የጦር ወንጀሎች ውስጥ ይካተታሉ። ነገር ግን አንዳንድ ግዜ፣ ድርጊቶቹ ዕድሉ በሚጠቀሙ ተራ ሰዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV)፣ 'በጦርነት ውስጥ የሚደረገው መድፈር' ከሚለው ሐረግ በላይ በጣም የሰፋ ነው። ቃሉ፡ ታጣቂዎች፣ የጦር ኃይሎች ወይም የመንግስት ኃይሎች የአካባቢያቸውን ህዝብ ለመቆጣጠር እና ተዋጊዎችን ለማበረታታት ወሲባዊ ጥቃት የሚጠቀሙባቸው ሁኔታዎች ያጠቃልላል። በወንዶች እንዲሁም በሴቶች እና በልጆች ላይ ይፈጸማል።

እነዚህ ወንጀሎች ለተጎጂዎች እና ለማህበረሰቦቻቸው አስከፊ ውጤት አላቸው፣ ምክንያቱም CRSV ማህበራዊ ግንኙነቶችን በመበጠስ፣ ሰዎች ድጋፍን እና ድጋፍን ከሚሰጡ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች እና ከጎረቤቶች እንዲርቁ እና እንዲገለሉ ስለሚያደርግ ነው። በተጨማሪም ከመደፈር በኋላ ለሚወለዱት ልጆች ለትውልድ ሊዘልቅ የሚችል ጉዳት አለው። ወደ የማያቋርጥ መገለል እና ተጨማሪ ዓመፅ ሊያመራ ይችላል።

## እንደ ጋዜጠኞች እና ፊልም ሰሪዎች ያለን ሚና

ብዙውን ጊዜ ተጎጂዎችን ለመጀመሪያ ግዜ የሚያነጋግሩ የመገናኛ ብዙኃን አባላት ሲሆኑ፣ ይህን የሚያደርጉ ራሳቸው ለአደጋ በማጋለጥ ጭምር ነው፣ የህዝብና የመንግስት ግብረመልስ የሚጠይቁ ጉዳዮች ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ ስራቸው ስለሆነ። ይህንን ሥራ የሚሠራ ማንኛውም ጋዜጠኛ ምንጮቹ ላይ ጉዳት ማድረስ አይፈልግም፣ አደጋው እንዳለ ግን ግልጽ ነው። ምንም እንኳን ቀና ዓላማዎች ቢኖሩት፣ በቃለ መጠይቅ እና በዘገባው ላይ የሚደረጉ ስህተቶች ተጎጂዎችን ዋጋ እንደሌላቸው እና ብዝበዛ እንዲሰማቸው ማድረግ ይችላል። እንዲሁም ምንጮችን እና ቤተሰቦቻቸውን ለሀፍረት አልፎ ተርፎም በአንዳንድ ሁኔታዎች አካላዊ ጉዳያት ሊያጋልጡዋቸው ይችላሉ።

© Dart Centre Europe

እ.ኤ.አ. በ 2018 አንድ ያልተለመደ ነገር ያከናወነ አንድ ዘገባ ታትሟል-በግጭት ዞን ውስጥ የ CRSV ሰለባ የሆኑትን ተጎጂዎች በመገናኛ ብዙሃን ቃለ መጠይቅ የማድረግ ልምዳቸው ምን እንደ ሆነ ጠየቀ። የተሰጡ መልሶች አሳሳቢ ነበሩ። ስማንያ አምስት በመቶ የሚሆኑት፡ በዳርርት ማእከል የታተመ እና ተጎጂዎችን ለመጠበቅ በሚሠራ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለጋዜጠኞች ተብለው የተዘጋጁት ሁለት ምርጥ የአሠራር መመሪያዎችን የሚቃረን አሰራሮች ያጋጠማቸው ነበሩ።[ሀ] በሪፖርቱ የተጠቀሱት ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

> የገንዘብ ወይም የእርዳታ ሰጦታ በመጠቀም፣ ያለፈቃድ ማንነትን መግለፅ፣ ወይም የአስገድዶ መድፈር እና የወሲብ ጥቃትን ልምዶቻቸው ዝርዝር ለመግለጽ ግፊት ማድረግ… ስለ ጥቃቶቹ፣ በጣም ግላዊ እና ለሴቶች ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወይም ጋዜጠኞች የሴቶችን ታሪኮች በማተም የያዚዲ ማህበረሰብን ለመርዳት በሚሰችላቸው ሁኔታ ላይ መሆናቸውን መጠቆም።[ለ]

የአደገኛ አካባቢ ሥልጠና- በከፍተኛ የአደጋ ሁኔታዎች ጋዜጠኞች የራሳቸው ደህንነት እንዲጠብቁ ማዘጋጀት- አሁን የተለመደ ነው፣ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሪፖርተሮች አሁንም ከአሰቃቂ ሁኔታ ተጎጂዎች ጋር ለመስራት ተገቢ ሥልጠና አያገኙም፣ ሊጠቀሙበት የሚችሉ መመሪያም ብዙ የለም።

## ለመሆኑ ጥሩ ዝግጅት ምን ይመስላል?

በማንኛውም የመዘገብ ጉዞ ላይ፣ በተለይም ወደ ከፍተኛ አደጋ ያለበት አካባቢ የሚደረግ፣ ጊዜ በጣም ወሳኝ ነው ፣ ስለዚህ ይህን ለማድረግ በሚቻልበት ወቅት ስለእነዚህ ነገሮች አስቀድመው ማሰብ ተገቢ ነው። ዝግጅት በሁለት ዋና ዋና መልክ ይካሄዳል፣ ሁለቱም ደግሞ ወሳኝ ናቸው፤

1. ለተለየ ተልእኮ በሚመደቡበት ወቅት ከበሩ ከመውጣትዎ በፊት ማድረግ ያለብዎት ዓይነት። ይህ አካባቢያውን ማጤን፣ የአደጋ ግምገማዎችን እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

2. ክህሎቶችን ለማዳበር የረዥም ጊዜ ቁርጠኝነት መኖር። ይህ ከስልጠና፣ ጉዳዮቹን ለመረዳት ቁርጠኝነት እና ከሌሎች የሥራ ባልደረቦች ጋር ግንዛቤዎችን ለማካፈል የመሰጠት እና የመውሰድ የተከፈተ ዓዕምሮ መኖር የሚመጣ ነዉ።

## ለተመደቡለት ልዩ ስራ የሚመለከት ዝግጅት

ለራስህ እና ለቡድንህ ደህንነት የአደጋ ምዘናዎችን የማካሄድ ልምድ ሊኖርህ ይችላል። (ከታች ያለውን የመረጃ ሳጥን ይመልከቱ።) በተመሳሳይ ጊዜ፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን (CRSV) በሚሸፍኑበት ጊዜ፣ ዘገባዎ ከእርሰዎ ጋር የሚሰሩትን የማንኛውም ምንጮች አካላዊ እና ሰነ-ልቦናዊ ደህንነትን እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ማሰብ አለብዎት።

መጠየቅ ያለብዎት ጥያቄዎች፡

- ስለራስዎ ደህንነት ብቻ ሳይሆን ቃለ ምልልስ ስለምታደርጉት ሰዎች ደህንነትም ጥሩ ውሳኔዎችን ማድረግ በሚያስችል ደረጃ የአካባቢ የስልጣን ተዋረድ እና በመሬት ላይ ያለውን የደህንነት ሁኔታ አጥንተውታል? [**ቁ.2** ይመልከቱ]።
- ከተጎጂዎች ጋር የሚያደርጉትን ቃለ መጠይቅ ማን ያመቻችልዎታል? አገናኝ፣ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይስ በአከባቢው የስልጣን ተጽዕኖ ያላቸው ወገኖች? መስማማታቸው በፈቃደኝነት ላይሆን የሚችልበት አደጋ አለ? [**ቁ.2** እና **ቁ.3** ይመልከቱ]።
- ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ማዕቀፋን ተረድተዋል – ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት አካባቢያዊ አመለካከቶች፣ በጾታ ላይ የተመሰረተ መድልዎ እና በቤተሰብ ውስጥ ያለውን የስልጣን አለመመጣጠን ጭምር? ለተሳታፊዎቹ ሊያስከትለው የሚችል አደጋ በሚገባ ተረድተዋል? [**ቁ.2** ይመልከቱ።]
- በአካባቢው ስላሉ የአካባቢ ህጎች፡ ይፋ ማድረጉ ከምንጮች ደኅንነት እና ተጨማሪ የፍትህ ዕርምጃ ለመፈለግ ባላቸው ችሎታ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አንድምታ ተገንዝቦውታል? (በአንዳንድ ክልሎች የአስገድዶ መድፈር ሰለባ መሆን ብቻ የዝሙት ክስ ሊቀርብ ይችላል።)
- ስለራስዎ የሰነ-ልቦና ዝግጁነትስ? አሁን ይህንን ስራ ለመስራት በግልዎ ጥሩ ሁኔታ ላይ ነዎት? [**ቁ.6** ይመልከቱ]።

---

**ሀ.** እነዚህ፣ ይህ **የዳርት ሴንተር** ለመጀመሪያ ጊዜ በ2003 ዓ.ም የታተመው መመሪያ እና በአንድ ‘ግሎባል ፕሮተክሽን ክላስተር’ ተብሎ የሚጠራ የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥምረት የታተመው፣ **በሰብአዊ ቀውስ ሁኔታዎች ውስጥ በሰርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ሪፖርት ለማድረግ የሚረዱ ተከታታይ መመሪያዎች ናቸው።**

**ለ.** ጆሃና ኢ. ፎስተር እና ሸሪዛን ሚናዋላ፣ ‘የያዚዲ ሴቶች ድምጽ፤ ስለ ‘በእስላሚክ ስቴት’ በተፈጸሙ ወሲባዊ ጥቃት በመዘገብ ላይ ስላሉ የጋዜጠኝነት አሰራሮች አስተሳሰቦች’፣ ‘ዉመንስ ስታዲስ ኢንተርናሽናል ፎረም 67 (2018)፤ 53-64።

## መደበኛ ዝግጁነት

አንዳንድ ሌሎች የዝግጅት ዓይነቶች ረዘም ያለ ግዜ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ወደ ስራ ከመስመራቱ በፊት በደንብ ታቅደው ቢቆዩ ይሻላል። እንዲሁ፣ በተዛማጅ ሥልጠና ላይ መሳተፍ ግድ ይላል፣ ካልሆነ ግን፣ እንደ ራሰዎ-ማሰተማር ወይም ከዕውቀት ካላቸው ባልደረቦች ውጤታማ ምክር ያሉ ሌሎች መንገዶች ሁሉንም ሊያግዙ ይችላሉ።

ራሰዎን ይህንን ይጠይቁ፤

- የምንጮችን ሰም-አልባነት ለመጠበቅ እና ጥድፊያዎችን ለመጠበቅ ብቁ የዲጂታል ደህንነት እቅድ አልዎት? [የመርጃ ሣጥን **ቁ.2**ን ይመልከቱ]።
- የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ጉዳተኞች ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሚረዱ ስልቶችን ለማግኘት ጥናት አድርገዋል? እዚህ ማወቅ ያለብዎት ልዩ ጉዳዮች አሉ። [**ቁ.4** እና **ቁ.5** ይመልከቱ]።
- ትርጉም ያለው ሰምምነት የሚለውን ሃሳብ ተረድተውታል፣ እንዴት ማቅረብ እንዳለቦትስ አሰበውበታል? [**ቁ.3** ይመልከቱ]።
- ቪድዮ ወይም ፎቶግራፍ የሚያነሱ ከሆነ፣ ሰም-አልባነቱ እንዴት እንደሚይዙት እና ተጎጂዎችን ብጥሩ ሁኔታ እንዴት ማሰተናገድ እንደሚችሉ አሰበውበታል? [**ቁ.8** ተመልከት]።

## አዘጋጆች ሊያሰቡበት ያላቸው ነገሮች

እነዚህ መመሪያዎች ለማዘጋጀት ባካሄድናቸው የምክክር ሂደት ወቅት ያነጋገርናቸው ሁሉም – አዘጋጆችም ሆኑ ሪፖርተሮች፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን (CRSV) የታዩባቸው እና ከእነርሱ ውጭ በሆኑ አገሮች – አዘጋጆች እና የፊልም ተልእኮ የሚሰጡ ሃላፊዎች ምንጮችን በመጠበቅ ረገድ ያላቸውን ሚና አጉልተዋል። በመሬት ላይ ያሉ ጋዜጠኞች በዘፍቃድ አይሰሩም: ተጠሪነታቸው ለህትመቶች ወይም ለብሮድካስተሮች ናቸው።

በጠረጴዛው እና በመሰክ መካከል ያለው ግንኙነት ግን ትልቅ ችግር ሊሆን ይችላል። በጣም ጥሩ በሆነው ሁኔታ፣ የዜና ክፍሉ ከክስተቶች ያለው ርቀት ዜናውን ከሰሜት በራቀ እንዲገመግም ያደርገዋል። ነገር ግን በነባራዊ ሁኔታን እና  በተጎጂዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ያለው ግንዛቤ እናሳ እንዲሆን ሊደርግም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በመሰኩ  ውሰጥ ያሉ ጋዜጠኞች የተከፈለ ተከፍሎ ዜናውን እንዲያገኙ ጫና አለባቸው።.

በተመሳሳይ መልኩ፣ አዘጋጆቹ በመሬት ላይ ስለሚሆነው ነገር ሙሉ ቁጥጥር የላቸውም። ጋዜጠኞች እና ፊልም ሰሪዎች ብዙውን ጊዜ በከፍተኛ ጫና ውስጥ እየሰሩ ናቸው እናም ብዙ ርቀት ተጉዘው በከፍተኛ የግል ሰጋት ውሰጥ ሊሆኑ ይችላሉ; ፍሪላንሰ ጋዜጠኞች ወደ ግጭት ቀጠና ለመድረሰ የራሳቸው ገንዘብ አውጥተው ሊሆን ይችላል። በነዚህ ሁኔታዎች ማዕዘኖች ሊቆረጡ ይችላሉ: ቃለመጠይቆች ከሚገባቸው በላይ ሊመዘመዙ ይችላሉ፣ በትክክል በመረጃ ላይ የተመሰረተ ሰምምነት ላይገኝ ይችላል፣ ወይም የተጎጂዎችን ሰም-አልባነት እንዳይጋለጥ ለመከላከል በቂ እርምጃ ላይወሰድ ይችላል።

የተሻለ ግንኙነት መፍጠር ከእነዚህ ብዙ አደጋዎችን ለማሰወገድ ይረዳል። ጋዜጠኞች የሚገጥምዋቸው የሰነምግባር ጉዳዮችን ከአዘጋጆች ጋር ማካፈል እንደሚችሉ ነጻነት ሊሰማቸው ይገባል። በተጨማሪ ዜናውን ለማግኘት ከህትመቱ አላማ በፊት የተጎጂዎችን አካላዊ እና ሰሜታዊ ደህንነት በማሰቀደማቸው ቅጣት እንደማይደርሰባቸው ሊሰማቸው ይገባል።

በመመሪያው ውስጥ እነዚህን ጉዳዮች በጥልቀት እንመረምራለን። ከዛ በፊት ግን: ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን (CRSV) ለመዘገብ ጋዜጠኞችን ለየሚያሰማሩ አዘጋጆች አጭር ማረጋገጫ ዝርዝር እነሆ:

- ጋዜጠኞች፣ ለአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር በሚሰሩበት ግዜ ሊከተሏቸው የሚገቡትን
- ህጎች ተወያይተዋል?
- የምንጮችን ማንነት እና ክብር ለመጠበቅ አሰፈላጊ ለሆኑ የእይታ ምርጫዎች በሚመለከት ተገቢ እቅድ አውጥተዋል? በዛን ጊዜ ለመወሰን ቀላል አይደለም።
- ይህንን ጋዜጠኛ ለዚህ ሰራ መመደብ አሁን ትክክል ነው? በተከታታይ ብዙ አሰቃቂ ሰራዎችን በመሸፈን ከመጠን በላይ የመጫን አደጋ አለው ወይ?

© Dart Centre Europe

- ጋዜጠኛው ከእርሰዎ ጋር ማንኛውንም የሰነምግባር ጉዳዮች መወያየት እንደሚችሉ ያውቃሉ?
- ጋዜጠኛው ይህን የመሰለ መረጃ አግኝተዋል?
- እና በመጨረሻም፣ ተጎጂዎችን እንዴት ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደሚቻል የሚመለከት ተገቢውን ስልጠና ለመስጠት አስበሃል? መጥፎ አጋጣሚ ሆኖ፣ ይህ በአብዛኛው የአደገኛ አካባቢ ስልጠና ውስጥ የሚካተት ነገር አይደለም። ከአሰቃቂ ክስተቶች ጋር በተያያዙ ስራዎች ላይ የሚሰማሩ ጋዜጠኞችን ለመደገፍ እና ለመጠበቅ ድርጅትዎ ምን ማድረግ እንደሚችል በዚህ **በዳርት ሴንተር ኤዥያ ፓሲፊክ** የተዘጋጀ መመሪያ ውስጥ ተጨማሪ ማግኘት ይችላሉ።

ክፍል **ቀ.7** እና **ቁ.8** ስለ ሕትመት እና ስርጭት ጉዳዮችን በበለጠ ዝርዝር ያብራራሉ።

## ተጨማሪ መረጃዎች፤ አጠቃላይ እይታ

በመጀመሪያ፣ ሁሉም ሰው **የሙራድ ኮድን** ረቂቅ እንዲያነብ እናበረታታለን። ይህ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን (CRSV) ተጎጂዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላለው ማንኛውም ሰው የምርጥ አሰራር መርሆዎችን አጥርቶ የሚያሳይ ተነሳሽነት ነው - ጋዜጠኛ፣ ጠበቃ፣ የወንጀል መርማሪ፣ ፖሊሲ አውጪ ይሁኑ ወይም መንግሰታዊ ያልሆነ ድርጅት ጠበቃ። ከተጎጂዎች እንዲሁም ከባለሙያ አካላት ጋር በጥልቀት የተደረገ የመመካከር ውጤት ነው።

የዳርት ሴንተር **የወሲብ ጥቃትን** ለመሸፈን ብቻ የሚያተኩር ክፍል በድረ-ገጹ አለው። እዚያ፣ አጠቃላይ እይታን የሚያቀርብ ይህን **የዳርት ሴንተር አውሮፓ** የምክር ገጾች ማግኘት ይችላሉ።

የአደጋ ግምገማ እና እቅድ መረጃዎች በክፍል **ቁ.2** ውስጥ ተካትተዋል።

ይህንን
ጽሑፍ ያጋሩ

እባክዎን በግራጫ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

# #2. ይህንን ሰው በዚህ ጊዜ እና በዚህ ቦታ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለብን?

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

# #2. ይህንን ሰው በዚህ ጊዜ እና በዚህ ቦታ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለብን?

የምንጮች ደህንነት መገምገም በሁሉም ደረጃ ያሉ ጋዜጠኞች ኃላፊነት ነው - በመሬት ላይ ያለው ዘጋቢ ይሁን፣ በዜና ክፍል ውስጥ ያለው አዘጋጅ እና ተመሳሳይ ዘገባ ለመሰራት የሚፈልጉ ባልደረቦች።

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV)ን በሚዘግቡበት ጊዜ ጋዜጠኞች ለራሳቸው እንደሚያደርጉት በምንጮቻቸው ደህንነት ላይ የአደጋ ግምገማ ማድረግ አለባቸው። ስለ ተገቢ ጥንቃቄ ያሉ ዋና ጥያቄዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤**

- **ይህንን ቃለ መጠይቅ ተገቢ ብሆነ መንገድ ለመምራት በቂ ጊዜ አለኝ? እነዚህ ንግግሮች በችኮላ መደረግ የለባቸውም። ካልሆነ፣ ምንም አይነት ጉዳት ላለማድረግ ነገሮችን በተለየ መንገድ እንዴት ማድረግ እችላለሁ?**
- **ይህ አካባቢ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው? በክፍሉ ውስጥ ያለው ማን ነው እና ማንስ ውስጥ መሆን የለበትም? በእኔ ምንጭ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ ለመገምገም የኃይሉን ተለዋዋጭነት በበቂ ሁኔታ ተረድቻለሁ? የማስገደድ ስሜት አለ?**
- **ይህ ሰው ለማነጋገር ትክክለኛው ሰው ነው? እሷ፣ እሱ ወይም እነሱ በስሜታዊነት በዚህ ጊዜ ለዚህ ውይይት በቂ የተረጋጋ ነው? ካልሆነስ ማን ሊሆን ይችላል?**

**ከፍተኛ የግል ስጋት በተመለከተ ረጅም ልምድ ሊኖርብዎት ይችላል፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የሁኔታው ስነምግባር አዲስ እቅድ ሊያስፈልግ ይችላል። አዘጋጆች ሆኑ በመስክ ላይ ያሉ ሰዎች ለዚህ ሃላፊነት መውሰድ አለባቸው - መነጋገር ጠቃሚ ይሆናል?**

## ይህን ለማድረግ በቂ ጊዜ አለኝ?

ጋዜጠኞች በስራቸው ከፍተኛ የጊዜ ግፊት አለባቸው። ነገር ግን የከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ተጎጂዎችን አሰቃቂነት ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ በቂ ጊዜ መስጠት አለቦት።

- ከተጎጂዎች ጋር ተገቢ በሆነ መልኩ ቁጭ ብለው ለመነጋገር ጊዜ ሊኖርዎት ይገባል.
- በቂ ጊዜ ከሌለዎት ቀንዎን እንደገና ማቀድ ይችላሉ?
- ቃለ-መጠይቁን በተለየ መንገድ ማድረግ ይችላሉ – ለምሳሌ፣ ስለያጋጠማቸው አሰቃቂ ዝርዝሮችን እንዲናገሩ ከመቸኮል ይልቅ በማስረጃ የተደገፉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ?
- በቀጥታ ካልተጠቃ ታማኝ ምንጭ ጋር መነጋገር ይችላሉ?

የዚህ ዓይነቱ እቅድ ከእርስዎ እና ከተጎጂዎች ውጭ ያሉ ሌሎች ሰዎችን ሊያካትት ይችላል። ቃለ መጠይቁ እንደ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም የአገር ሽማግሌዎች ቡድን በመሰለ አማላጅ በኩል እየተዘጋጀ ከሆነ፣ አቀራረባችሁን በዚሁ መሠረት ማቀድ እንዲችሉ ምን ያህል ጊዜ እንደሚኖሮት ከአዘጋጁ ጋር ይነጋገሩ።

በተቻለ መጠን በዚህ እቅድ የማውጣት ሂደት ተጎጂዎችን ማካተት አለቦት። የእራስዎ የጊዜ ሰሌዳ ተለዋዋጭ ከሆነ፣ በተለይ ስለሚያስለች ጉዳይ ለማውራት ብዙ ጉልበት ሊኖራቸው የሚችልበት ጊዜ ካለ አስቀድመው ጠይቋቸው። ተለዋዋጭነትን ወደ ምንጩ መመለስ ታሪካቸውን ለማካፈል የተወሰነ ቁጥጥር እንዳላቸው እንዲሰማቸው በማድረግ ረገድ ቀላል ግን ኃይለኛ መንገድ ነው።

© Dart Centre Europe

## ይህ ቦታ ለቃለ መጠይቅ አስተማማኝ ነው?

በምትሠሩባቸው አካባቢዎች ስለሚኖር አካላዊ ደህንነት ለማሰብ ተለማምደው ይሆናል። ነገር ግን ተጎጂዎችን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ እቅድ ካልዎት፣ ይህን ሃሳብዎ ወደ ላቀ ደረጃ መውሰድ አለብዎት። በክፍሉ ውስጥ ያለው ማን ነው እና ለምንን የሚሉ አንዳንድ ቀላል ጥያቄዎችን እራስዎን በመጠየቅ ይጀምሩ፡

- የማህበረሰብ ሽማግሌዎች፣ ባለስልጣኖች ወይም ጠመንጃ ያላቸው ሰዎች አሉ?
- ከወንጀለኞች ጋር በሚገናኝ መረብ አካል የሆኑ ሰዎች አሉ?
- እዚያ መገኘት የማያስፈልግ ሰው አለ?

የጥቃት ፈጻሚዎች በክፍሉ ውስጥ ባይኖሩም በህብረተሰቡ ውስጥ እየኖሩ ነው? ስለ ቃለ መጠይቁ ሊሰሙ ይችላሉ? ቦታው ምን ያህል ገለል ያለ ነው? ጉዳተኞች ከማህበረሰቡ፣ ከቤተሰብ አባላት እና ከመሳሰሉት ወገኖች ሊገጥማቸው የሚችለው ተጨማሪ መገለሎችን ለማስወገድ ምን ማድረግ ይችላሉ?

ምን እየሰሩ እንደሆነ በትክክል ካላወቁ በስተቀር ሰዎችን ዓመጹ ወደ የተፈጸመበት ቦታ አይውሰዱ። የቦታ እና የእይታ ትውስታዎች ከፍተኛ የስሜት ቀውስ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ምንም እንኳን እንደዚህ አይነት ሁኔታን ለማስታረቅ አስቸጋሪ ሊሆን ቢችልም, ቃለ-መጠይቁን እርስዎ የሚቆጣጠሩት እንደሆኑ ያስታውሱ። ስለዚህ የተገደዱ መስለዉ ከታዩ, ወይም ተጎጂዎችን አደጋ የሚያስከትል ከሆን ወደ። መቀጠል የለብዎትም። አዘጋጆችም እዚህ ላይ ሚና አላቸው፣ ምክንያቱም ጋዜጠኛው የስነምግባር ፈተና በሚገጥመው ግዜ ከዜና ክፍል የሚመጣ ግፊት አእምሮው ላይ ስለሚመዝን።

ከእርስዎ ጋር የመጡ ሰዎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡-

- አስራጭ ከሆኑ የረዳተችዎን ቁጥር አነስተኛ ማድረግ ይችላሉ?
- ከፎቶግራፍ አንሺ ጋር እየሰሩ ከሆነ, ተጎጂውን ስለ አስቃቂ ክስተቶች ሲናገር በተመሳሳይ ጊዜ ፎቶግራፍ እንዳይነሳ ለማድረግ፡ ፎቶግራፎቹን በተለየ ግዜ ወይም ከቃለ መጠይቁ በኋላ ማንሳት ይችላል?
- ከአስተርጓሚ ጋር እየሰሩ ከሆነ, ለሥራው ትክክለኛ ሰው ናቸው? ጉዳዮቹን ተረድተዋል? ስለ አስቃቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ቃለ መጠይቅ ገለጻ ተሰጥቷቸዋል?
- ተጎጂው በክፍሉ ውስጥ ከተቃራኒ ጾታ ካላቸው ሰዎች ጋር መነጋገር ምቾት ይሰማዋል? ሴቶች ሴቶችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ወይም ወንዶች ለወንዶች ቃለ መጠይቅ ማድረግ የግድ አስፈላጊ አይደለም፣ ነገር ግን ይህ ግምት ውስጥ የሚገባ ነው።
- ከተቻለ ተጎጂዎችን ምን እንደሚያመቻቸው ይጠይቁ። ከሳቸው ጋር እንዲሆን የሚፈልጉት እንደ ዘመድ ወይም ታማኝ ወዳጃቸው ሰው አለ? ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ቃለ መጠይቅ እያደረጉ ከሆነ፣ ሞግዚታቸው **ሁል ጊዜ** መገኘት አለበት። (ስለ ወሲባዊ ጥቃት ልጆችን እና ወጣቶችን ቃለ መጠይቅ ማድረግ የተወሰኑ ክህሎቶችን እና ተጨማሪ ትጋትን ይጠይቃል። ይህ በእርግጥ ማድረግ ያለብዎት ነገር እንደሆነ እራስዎን ይጠይቁ።)

## ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ትክክለኛው ሰው ይህ ነው?

እነዚህን ቀላል ጥያቄዎች ይጠይቁ፡-

- ይህን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ያስፈልጎታል? የሚጨምረው ነገር አለ ወይም አስቀድሞ ያገኙት በቂ መረጃ አለ?
- ተጠያቂዎች ምን እንደሚጠበቅባቸው በሚረዱበት ሁኔታ ናቸው ያሉት?
- የተደበቁ ተስፋዎች አሉ? ከእውነታው የራቁ ያልሆኑ ከእርስዎ ጋር በመገናኘት ውጤቱን እየጠበቁ ነው?
- የሆኑ የተደበቁ ተስፋዎች አሉ? ከእርስዎ ጋር በመገናኘታቸው ከእውነታው የራቁ ውጤቶች እየጠበቁ ነውን?

ብዙ ጊዜ በግጭት ወይም ከግጭት በኋላ ባሉ ሁኔታዎች፣ በመሬት ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጋዜጠኞች መዳረሻ ናቸው፣ እና እርስዎ ከፆታዊ ጥቃት የተረፉ ሰዎችን እንዲያነጋግሩ የሚያዘጋጁት እነሱ ሊሆኑ ይችላሉ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አንድ ሰው ወይም ትንሽ ቡድን ከጋዜጠኞች ጋር በሚያጨናንቅ ቃለ ምልልስ እንዲሳተፉ በማድረግ የሚያዘጋጁበት ሁኔታ ሊገጥሞት ይችላሉ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ታሪኩን ደጋግሞ መናገር አስቃቂ ጉዳት ለደረሰበት ሰው በጣም የሚያስጨንቅ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በተረፈው ላይ ህጋዊ መዘዝ ሊኖረው ይችላል። የሰጡት የተለያዩ ቃለ መጠይቆች በጥቂቱ የሚቃረኑ ከሆነ፣ በኋላ ላይ የሕግ ዕርምጃ የመፈለግ እድላቸውን ሊያሳጣው ይችላል [ሳጹን **ቁ.3** ይመልከቱ]።

© Dart Centre Europe

ጋዜጠኞች ካላቸው ጫና አንፃር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሚሰጡት ምክር ጋር አብሮ መሄድ ቀላል ነው። ነገር ግን ቃለ መጠይቅ በሚያደርጉት ማንኛውም ተጎጂ ላይ ስለሚኖሩ ጫናዎች ውይይት ማድረግ ጠቃሚ ነው። ምን ያህል ጊዜ ቃለ መጠይቅ እንደተደረገላቸው መጠየቅ ሊሆን ይችላል። እና በፈጠራ አስቡ – በጋዜጠኞች ቡድን ውስጥ እየተጓዙ ከሆነ፣ ተጎጂዎችን ታሪካቸውን አንድ ጊዜ ብቻ እንዲያካፍሉ ጥናቶቻቹህ በአንድ ማስባሰብ ይቻላል?

እ.ኤ.አ. በ2019፣ የሂዩማን ራይትስ ዎች ሰራተኛ የሆነች ስካይ ዊለር በ'ኮሎምቢያ ጀርናሊዝም ሪቪው' የተባለ መጽሔት እንደጻፈችው በባንግላዲሽ በሚገኙ የሮሂንጊያ የስደተኞች መጠለያ ካምፖች ከሚገኙ የፆታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎች የተደረገ ስነ-ምግባር የጎደለው ጋዜጠኝነትና እና የምርምር አሰራሮች ላይ አንፀባርቃለች፡-

> "ያለ ጥርጥር፣ ወደ ኋላ መለስ ብለን ሰናስብ ነገሮች ጥሩ አልነበሩም ማለት እንችላለን።
> ሰዎች በጣም ብዙ ጊዜ በድጋሚ ቃለ መጠይቅ ተደርገዋል [ሀ]።

ዋናው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ – ለመፍረድ ከባድ ሊሆን እንኳን ቢችል – አንድ ሰው ቃለ መጠይቅ ለመስጠት በቂ የስነ-ልቦና ደህንነት ይሰማው እንደሆነ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ከአሰቃቂ ሁኔታ በኋላ በተለይ ከፍ ያለ የጭንቀት ደረጃ እያጋጠመው ከሆነ፣ ደህነት የማይሰማቸው ሊሆኑ ይችላል። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ብዙ ግዜ ለብቻው የሚከሰት አለመሆኑን አይርሱ – ተጎጂዎች በቅርብ ጊዜ ሌላ ዓይነት ጥቃት የደረሳቸው፣ የቤተሰብ አባላት መጥፋት ወይም መፈናቀል ያጋጠማቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

የምንጭዎ እንዲሁም የእራስዎን ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነት ለመገምገም ማሰብ ከባድ ሊሆን ይችላል። መፍትሄው ብዙውን ጊዜ ሰዎች ቃለ መጠይቁ ምን እንደሚመስል እንዲወስኑ እና እንዴት እንደሚካሄድ ላይ የተወሰነ ቁጥጥር እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። አብዛኛዎቹ እነዚህ ጉዳዮች ከየፈቃድ ስምምነት ጥያቄ ጋር የተዛመዱ ናቸው – ይህን በተመለከተ ተጨማሪ በክፍል **ቁ.3**።

## መገለል እና እንዴት ዘገባው ወደ መጥፎ ነገር ሊያመራ እንደሚችል

ወደ አንድ ሰው መቅረብ ደህንነታቸውን እና ግላዊነትን አደጋ ላይ ይጥላል እንደሆነ ራስዎን ይጠይቁ። በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ፣ ተደፍረዋል ተብሎ መጠርጠራቸው ብቻ ውርደትን፣ መገለልን ከዛም አልፎ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።

ጋዜጠኞች በመስክ ላይ ስላለው ነባራዊ ሁኔታን ሙሉ ግንዛቤ ካላገኙ ነገሮች እንዴት ሊበላሹ እንደሚችሉ የሚያሳይ ከኢራቅ የተወሰደ ምሳሌ እዚህ ቀርቧል።

ዮሃና ፎስተር እና ሼሪዛን ሚንዋላ በተከታታይ 26 ቃለመጠይቆች በማድረግ የያዚዲ ሴቶች ስለ በአይሲስ (ISIS) እጅ የግዞት፣ መደፈር እና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ በሆኑ ሴቶች እና ልጃገረዶች የተደረገ የሚዲያ ዘገባ ምንነት እና ተፅእኖ ያላቸውን ግንዛቤ ዳሰሰዋል። ውጤታቸውን እ.እ.አ በ2018 በወጣ የምርምር ወረቀት ላይ አሰቀምጠዋል። የሚከተሉት አንዳንድ ቁልፍ ቀመሮች ይመልከቱ፤

> በአለም ላይ እንዳሉት ሌሎች ሴቶች፣ የያዚዲ ሴቶች ከራሳቸው ይልቅ የማህበረሰቡን ፍላጎት እንዲያስቀድሙ የሚጠይቅ የተለመደ የስርዓተ-ፆታ ችግር ገጥሟቸዋል።
>
> በተለይም፣ ምንም እንኳን የራሳቸው አካላዊ፣ ክብር እና ስሜታቸው የመጎዳት አደጋዎች ቢኖሩም አሰቃቂ ታሪኮቻቸውን ለዓለም ለመሰጠት መሰዋዕትነት ለመክፈል ውሳኔ ገጥሟቸዋል። በእርግጥ የያዚዲ ሴቶች ይህን እንዲያደርጉ በያዚዲ ወንዶች በቀጥታ ተበረታተው ነበር… ምንም እንኳን ክብራቸውን በማጣታቸው እንደማይገለሉ ወይም በቤተሰቦቻቸው እና በማህበረሰባቸው መጥፎ አያያዝ እንደማይደረግላቸው ወይም ተቀባይነት እንደማያጡ እውነተኛ ማረጋገጫዎች ቢኖሩም፣ በተለይም በጊዜ ሂደት።

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የያዚዲ ሴቶች አንዷ እንዲህ ብላለች፡-

> "መጀመሪያ ላይ [ከአይሲስ] ስመለስ አንድ ኮሚቴ መቅጃ ይዞ መጥቶ ታሪክሽን እንመዘግባለን ሲለኝ 'አይሆንም' ሰላልኩኝ ወደ የባሌ ወንድም ሄደው 'ከኛ ጋር ማውራት እምቢ ብላለች' ብለው ነገሩት።'"
>
> ተጨማሪ የማስገደድ ደረጃዎችን በማከል፣ የያዚዲ ሴቶች በሚተማመኑባቸው ካምፖች ውስጥ ይኖሩ ነበር፣ እና የሰብአዊ አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የካምፕ ሰራተኞችን እና ጋዜጠኞችን ለማሰደሰት ባለው ዕዳ ወይም ግዴታ ተሰምቷቸው ነበር ሁሉም የተረፉት ታሪካቸውን እንዲናገሩ ተጨማሪ ጫና ያደርጉ ነበር።

**ሀ.** ይመልከቱ፡ **https://www.cjr.org/analysis/rohingya-interviews.php**

**ለ.** ጆሃና ኢ. ፎስተር እና ሸሪዛን ሚንዋላ፣ የያዚዲ ሴቶች ድምጽ፤ ስለጋዜጠኝነት አሰራር ያሉ እይታዎች በአይሲስ የወሲብ ጥቃቶች ዘገባዎች፡ *Women's Studies International Forum 67 (2018): 53–64.*

© Dart Centre Europe

> የያዚዲ ሴቶች በመጠለያዎች ውስጥ በሚኖሩበት ወቅት የሰብአዊ አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የካምፕ ሰራተኞችን እና ጋዜጠኞችን በተጎጂዎቹ ተጨማሪ ጫና ያደርጉ ስለነበር ዕዳ ወይም ግዴታ ተሰምቷቸው እነሱን ለማስደሰት ታሪካቸውን እንዲናገሩ ተጨማሪ አስገዳጅ ሁኔታ ገጥሞዋቸዋል።

“ያዚዲ ሴት በአይሲስ ለሦስት ወራት ያህል የወሲብ ባሪያ ሆና ተይዛ የነበረችና በቡድን የተደፈረች ስለደረሰባት አሰቃያሚ ሰቃይ ትናገራለች፣ “የአይሲስ የወሲብ ባሪያ ሴት ልጆችን ‘በትንሽ ሲጋራ’ ሳይቀር ይሸጣሉ” እና “የያዚዲ ሴቶች በዳዒሽ ከተደፈሩ በኋላ ‘ድንግልናን ለመመለስ’ ቀዶ ጥገና ይደረግላቸዋል” የሚሉ የዜናዊ ዘገባ እንደሚከተሉት በመሳሰሉት ስሜት ቀሰቃሽ አርዕሰተ ዜናዎች ሲወጡ የመገለል እድልን ከፍ አድርጎታል። [^]

## ተጨማሪ መረጃዎች፤ ደህንነት

አደገኛ የሰራ ሰምሪቶች ላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚመለከቱ በመገናኛ ብዙሃን ድጋፍ እና ጥበቃ ድርጅቶች በሚታተሙ የተለያዩ መመሪያዎች አሉ። በ’**ሲፒጄ**’ (የጋዜጠኞች ጥበቃ ኮሚቴ)፣ ACOS Alliance (የደህንነት ባህል) እና **የሮሪ ፔክ ትረሰት** (ለግል ጋዜጠኞች ተብሎ የተዘጋጀ) አጠቃላይ እይታዎችን በመመልከት እንዲጀምሩ እንመክራለን፣ ነገር ግን ሌሎች ብዙ ጠቃሚ ምንጮችም አሉ። (ከዛም አልፎ እነዚሁ ድርጅቶች ስልጠና ማግኘት እና ሌሎች አይነት ድጋፎችን በተመለከተ ምክር ሊሰጡ ይችላሉ።)

**ደህንነት እና ጥበቃ (Safe and Secure)** ከ’ዶክ ሶሳይቲ’ ለፊልም ሰሪዎች ተብሎ የተነደፈ ነው። ስለ አካላዊ ደህንነት ጠቃሚ ምክሮችን ከመሰጠት በተጨማሪ የቡድን አባላትን እና አስተዋፅዖዎችን ከህጋዊ እና ዲጂታል የደህንነት ስጋቶች ለመጠበቅ ለማንኛውም ጋዜጠኛ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጠቃሚ ምክር ይሰጣል - ሁለት ብዙውን ጊዜ ችላ የተባሉ ወሳኝ ገጽታዎች። ‘ግሎባል ኢንቬስትጌቲቭ ጋዜጠኝነት ኔትወርክ’ም ይህንን **ዝርዝር የመረጃ ድህረገፅ** ያቀርባል።

አዘጋጅ ወይም ሰራ አስኪያጅ ከሆኑ ድግሞ፣ ለዜና **ድርጅቶች የተዘጋጀ ACOS የደህንነት መገምገሚያ መሳሪያ** እና የዳርት ማእከል **ለአሰቃቂ ሁኔታ ከተጋለጡ ከነፃ ጋዜጠኞች ጋር እንዴት መሰራት እንደሚቻል** የሚገልጽ መመሪያን ይመልከቱ። የሲፒጄ ባልደረባ የሆነው **ፍራንክ ስሚዝ** ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) በሚዘግቡ ጋዜጠኞች ላይ ስለሚችሉ አደጋዎች የሚመለከት ማብራሪያ ጽፏል።

ይህንን
ጽሑፍ ያጋሩ

እባክዎን በግራጫ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

# #3.

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

# ቃለመጠይቅ የማደርግላቸው ሰዎች በመሳተፋቸው ሊደርስባቸው የሚችል መዘዝ ሙሉ በሙሉ ተረድተዋልን?

# #3.

ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

## ቃለመጠይቅ የማደርግላቸው ሰዎች በመሳተፋቸው ሊደርስባቸው የሚችል መዘዝ ሙሉ በሙሉ ተረድተዋልን?

አንድ ሰው ምስክርነቱን እንድትጠቀሙ ወይም ምስሉ እንዲነሳ ፈቃደኛ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም። ሙሉ በሙሉ ግንዛቤ ካላገኘ በስተቀር የፈቃድ ስምምነቱ ትርጉም የለውም።

**አንድ ሰው ለመናገር ተስማምቷል ወይም ምስሉን እንዲታይ ፈቅዷል ማለት፣ ምን እንደሚያጠቃልል በትክክል ያውቃል ማለት አይደለም። እርሰዎ ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ለአንድ ሰው መንገር በቂ አይደለም። አደጋዎቹን እንዲረዱ እና እውነተኛ ምርጫዎች እንዲኖራቸው ለማድረግ የበለጠ ርቀት መሄድ ይኖርብዎታል። በተለይም ማወቅ ያለባቸው፦**

- **የቃለ መጠይቁ ወይም የቀረጻው ሂደት እንዴት እንደሚሰራ።**
- **የትኞቹን ታሪኮች እና ገጽታዎች ለመወያየት እንዳሰባችሁ ነው።**
- **መረጃዎችን ማን ማየት እንደሚችል እና ለምን ያህል ጊዜ ሊቆይ እንደሚችል**

**የፈቃድ ስምምነትን ማግኘት ዕድል እንጂ መወጣት የሚያስፈልገው እንቅፋት አይደለም። ምንጭዎ ስጋቶቹን የሚያውቅ ከሆነ እና ሙሉ በሙሉ ከተስማማ የበለጠ ውጤታማ ቃለ መጠይቅ ያገኛሉ።**

የቃለ መጠይቁን የፈቃድ ስምምነት ለማግኘት የተለመደው የጋዜጠኝነት አብነት ዘጋቢዎች፣ ታዋቂ ሰዎች ቃለ መጠይቅ ከሚያደርጉበት ሁኔታ የመነጨ ነው። እነዚህ ግን ብዙውን ጊዜ በለመዱት ጨዋታ ውስጥ የተቀመጡትን ህጎች የሚረዱ ጠንካራ ሰዎች ናቸው። ዋናው ትኩረት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ እና ፖለቲከኛውን ወይም ነጋዴውን በተቻለ መጠን ስማቸው በግልጽ ተጠቅሞ እንዲናገሩ ማድረግ ነው።

ከተጋላጭ ሰዎች በሚሰሩበት ግዜ ግን፣ በጋዜጠኛው እና ምንጮች መካከል ያለው የኃይል ሚዛን በግልባጩ ስለሚሆን ያንን ሞዴል መጠቀም ትክክል አይደለም። በተጨማሪም፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) በሚከሰቱበት ሁኔታዎች ውስጥ መጀመሪያው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት የምንጩን ስም-አልባነት ጥበቃ መሆን አለበት። ይህ ማለት ተጎጂው ሰው በይፋ የመናገር ግዴታ አለበት የሚለውን ግምት ወደ ጎን መተው ማለት ነው።

በመጀመርያ ደረጃ ይህ ግልጽ ነው። እያንዳንዱ ጋዜጠኛ ይህን ያውቃል (ወይንም ማወቅ አለበት)። በሌላ ደረጃ፣ የፖለቲካ ሞዴል ትሩፋት ስር የሰደደ በመሆኑ አሁንም ጋዜጠኞችን ማጥመድ ይችላል። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ላይ እየዘገቡ ከሆነ፣ ቆም ማለት እና ትርጉም ያለው ስምምነት ተብሎ ሊጠራ ከሚችል ሌላ መነሻ መጀመርዎን ማረጋገጥ እንዳለቦት ማሰብ ይኖርብዎታል፤

1. በመጀመሪያ፣ በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ ስምምነት በዋነኛነት መግቢያ ለማግኘት እና አንድ ሰው ለቃለ መጠይቅ እንዲሰማማ ማድረግ ነው የሚለውን ሃሳብ ወደጎን ይተዉ፤ አይደለም። ከፍተኛ አደጋዎች ባለበት ግንኙነት እንዴት አንድ ሰው የበለጠ አስተማማኝ መሰረት ያለው ደህንነት እንደሚገነባ ማሰስ ነው። አንድ ሰው ሀሳቡን ከቀየረ እና መናገር እንደማይፈልግ ግልጽ ከሆነ፣ ያንን እንደ ጥሩ ውጤት ይውሰዱት። ልክ የሙከራ ፈተና ውስጥ እንደሚሆነው፣ ለዚህ ሚና ትክክል አይደሉም ማለት ነው።

2. ሁለተኛ፣ ስምምነትን ማግኘት የአንድ ጊዜ ተግባር እና፣ ልክ በውይይት መጀመሪያ ላይ የሚከሰት ህጋዊነት ያለው ደንብ አይደለም። ቀጣይነት ያለው ሂደት፣ በልዩ ዝርዝሮች ላይ ወይም በአጠቃላይ ውይይቱ የመዘገብ መብት ለማግኘት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊጎበኝ የሚችልበት ድርድር ነው።

አንድን ሰው እንደ ወሲባዊ ጥቃት ያለ የጠበቀ የግል ጉዳይ እንዲናገር በጭራሽ አያስጨንቁ ወይም አያታልሉት። ነፃ እና ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ ምርጫ መሆን አለበት።

© Dart Centre Europe

## ማን የፈቃድ ስምምነት መስጠት ይችላል?

ፈቃድ መስጠት የሚችለው ብቸኛው ሰው ባለጉዳዩ (ተጎጂው) ነው። ግለሰቡ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወይም በሆነ መንገድ ሙሉ በሙሉ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፍርድ ለመስጠት የማይችል ሰው ከሆነ፣ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ከሆነ ሰው ተጨማሪ ስምምነት ሊያስፈልግ ይችላል።

ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ፣ **ከተጠያቂው ትርጉም ያለው የፈቃድ ስምምነት ካልተሰጠዎት – ፈቃድ የለዎትም።** የአንድ ዘመድ፣ የአንድ ሰው ጠበቃ፣ አገናኝ ወይም የተቀባይነት ያለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት አማላጅ ቃል የፈቃድ ስምምነትን አያመለክትም። ድርድሩ በቀጥታ ከምንጩ ጋር መሆን አለበት።

ከአስተርጓሚ ጋር እየሰሩ ከሆነ፣ ከምንጩ ጋር የሚያደርጉት ውይይት እርስዎ እያደረጉት ያሉት ነው ብለው የሚያስቡትን መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት። ይህ፣ ጋዜጠኛ ጂና ሙር እንደገለጸው ችግር ሊፈጥር ይችላል። ተጨማሪ እርምጃዎችን ሊወሰድ ይችላል። ለአስተርጓሚዎ መንገር ያለብዎት፡-

> “እራሴን በመድገሜ ይቅርታ፣ ነገር ግን አላማዬ ግልፅ መሆኑን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ፤ እኔ ማን እንደሆንኩ እነሆ። እኔ እየሰራሁት ያለሁት ይኸው ነው…” ተርጓሚው “እሱማ አስቀድሜ ጠየቅኳት” ብሎ ከተናገረ እርስዎ “አመሰግናለሁ፣ ግን የስራዬ ደንብ ራሴን በቀጥታ እንድጠይቃት ያስገድደኛል” ብለው “ስለዚህ፣ ካላስቸገርኩህ ይህንን ለመጨረሻ ጊዜ ለማረጋገጥ እንድንችል የምናገረውን ተርጉምልኝ…” ይበሉ።[U]

የስልጣን ባለቤትነቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ ተጎጂዎች ለእነርሱ ጥቅም በማይሰጥበት ወቅት እንዲናገሩ ግፊት ሊደረግባቸው ይችላል። እንደ ጋዜጠኛ፣ አንድ ሰው እውነተኛ ምርጫን ተጠቅሞ ፈቃድ ለመስጠት ይችላል ብሎ ከመገመትዎ በፊት ሁሉንም የተጋላጭነት ገጽታዎች በጥልቀት የመመርመር ግዴታ አለብዎት።

ከጥቃቱ በኋላ ባለው አጭር ግዜ (በተለይ ከደቂቃዎች እና ሰዓታት፣ ምናልባትም ከቀናት በኋላ) ውስጥ ተጎጂው ትርጉም ያለው ስምምነት ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ መሆኑ የሚጠበቅ ነው። የማናቸውም ተጎጂዎች ማንነት መለየት እንደማይቻል እርግጠኛ ከሆኑ፣ ስለሁኔታው የጀርባ መረጃን በመጠቀም የተከሰተውን ነገር የመዘገብ መንገድ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ያለ አንድ ሰው ስማቸው እንዳይገለጽ መብቱን ለመተው ወይም ላለመስጠት ውሳኔ ለማድረግ እንደማይችል ግልጽ ይሁኑ። ያ ከጥቃቱ የበለጠ ርቀት ያስፈልገዋል።

## ከአስተርጓሚዎች ጋር መሥራት

እርስዎ በማይኖሩበት አካባቢ እየሰሩ ከሆነ፣ ቋንቋውን ከሚናገሩ እና የመሬቱን አቀማመጥ ከሚያውቁ የሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች እና ተርጓሚዎች ጋር ያለዎት ግንኙነት ወሳኝ ነው። ነገር ግን እነሱ የስሜት-ቀውስ ሁኔታን ንቃት አላቸው ብለው ማሰብ አይችሉም።

የሚተረጉም ሰው የሚከተለውን መረዳቱን ማረጋገጥ አለቦት፡-

- ርዕስ ጉዳዩ ስሜትን የሚፈትን ሊሆን ይችላል።
- በምንጮች ላይ ጫና ማድረግ ወይም እንዲናገሩ ማበረታቻ ማቅረብ የለባቸውም።
- በግንዛቤ ላይ የተመሰረተ የፈቃድ ስምምነት እና የስሜት-ቀውስን ግምት ውስጥ ያስገባ የቃለ መጠይቅ አቀራረቦችን መጠቀም አለባቸው። (እዚህ መመሪያ ያሉ መረጃዎችን አሳዩዋቸው)
- ወደ ጭንቀት መግፋት ወይም ያለምክንያት ዝርዝር ምርመራ ማድረግ የለባቸውም።

ቃለ መጠይቅ እንዴት እንደምታደርግ የምትችለውን ያህል አስቀድመህ በዝርዝር ማቀድ አለብህ፣ የምታደርገውን እስከ መለማመድም ሊሆን ይችላል። ስለአደጋዎች እና ስለአካባቢው ባህላዊ ደንቦች ጥልቅ ውይይት ያድርጉ። እርስዎ እንዴት እየሰሩ እንደሆነ እና ለእርስዎ መተርጎም አስቸጋሪ ሆኖባቸው እንደሆነ አስተያየት እንዲሰጡዎት አስተርጓሚዎን ይጠይቁ።በግንኙነትዎ ላይ የበለጠ መተማመን የተሻለ ይሆናል። እንዲሁም በግል እንዴት እንደሆኑ እና በራሳቸው ወይም በቤተሰቦቻቸው ላይ ምንም አይነት አደጋ እንዳይኖር ማረጋገጥ አለብዎት።

[U] In Moore's article: Five ideas on Meaningful Consent in Trauma Journalism

© Dart Centre Europe

## የፈቃድ ስምምነትን ትርጉም ያለው የሚያደርገው ምንድን ነው?

አንድ ሰው ለመናገር ስለተስማማ፣ ያ ማለት ምን እንደሚያካትት በሚገባ ተረድተዋል ማለት አይደለም።

ስለ ሂደቱ፣ ምን ሊጠይቋቸው እንደሚፈልጉ እና ይህ ምን ያህል ጭንቀት ሊሆን እንደሚችል፣ እና በእነርሱ አስተዋጽዖ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ግልጽ ላይሆንላቸው ይችላል። ሀሳቡ፣ የሆነ ወደ ፊት ላይ የበለጠ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ያልተጠበቁ ነገሮችን ማስወገድ ነው። እርስዎ እና ቃለ-መጠይቅ የሚያደርጉት ሰው ስለሚከተሉት ነገሮች ግልጽ መሆናችሁን ያረጋግጡ፡-

- የውይይቱ አላማ ምን እንደሆነ?
- ማንን ይሳተፋል?
- ማውራት የማይፈልጉባቸው ‘የማይነኩዋቸው ነገሮች’ ካሉ።
- ዘገባው ማን ያየዋል (እና በአለም ላይ በየትኛውም ቦታ በበይነ መረብ በኩል ያለውን ተደራሽነት)።
- ፊልም ከሆነ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ እና እንዴት እንደሚከፋፈል
- ማንነታቸው እንዳይገለጽ እንዴት ይጠበቃል።
- በኢንተርኔት የጥቃት ሰለባ የሚሆኑበት ዕድል መኖር አለመኖሩን

ምስሎችን የሚጠቀሙ ከሆነ ተጠያቂውን በምስሎች ላይ በሚደረጉ ውሳኔዎች ማሳተፍ እና አለም ስለራሳቸው እና የሚኖሩበት ማህበረሰብ ምን እንደሚያይ ማሳየት ጥሩ ልምምድ ነው። የያዚዲ ሴቶች በአይሲስ መደፈራቸውን የሚዘግቡ ጋዜጠኞች ሴቶች ፊታቸውን ተከናንበው ፎቶግራፍ በማንሳት ስማቸው እንዳይገለጽ ዋስትና የሰጡ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን ሴቲቱ እራሳቸው ከዓይኖቻቸው እና በጣም ከሚለዩት ነጠላ መካከል አንዱ ሌላውን በግልፅ መለየት ይችላል. [**ቁ.8** ይመልከቱ።]

ጥልቅ፣ ግልጽ ያልሆነ የትጋት ደረጃዎች ሊያስፈልግ ይችላል – ለምሳሌ በእነዚህ በጣም ከባድ ጉዳዮች ግልጽ ካልሆኑ፡-

- ፊልሙ ወይም የመጨረሻ ዘገባው የወንጀለኞችን ወይም የሚደግፏቸውን ቡድኖች ድምጽ ያካትታልን? ከእውነታው በኋላ ይህንን ማወቁ መረጋጋትን ሊያሳጣ ይችላል። አንድ ተጎጂ ‘መልስ የመስጠት መብት’ የሚለውን መርህ እና እንዴት ማንም ሰው ጥቃት ፈጻሚዎችን ሃሳባቸው እንዲሰጡ ዕድል እንደሚሰጥ በመረዳት ረገድ ትልቅ ችግር ሊኖረው ይችላል። ይህንን ቀደም ብሎ ማብራራት ይሻላል።
- እርስዎ ያላነሱት የተደበቁ ተስፋዎች አሉ? ቃለ መጠይቅ የተደረገለት እርስዎን በማነጋገራቸው ለህብረተሰቡ ቀጥተኛ እርዳታ እንደሚያመጣ ያምናል? ወይም እርስዎ ሊሰጡት ማይችሉበት ለቀጣይ የስነ-ልቦና ድጋፍ ወይም ጓደኝነት ከእርስዎ ይጠብቃሉ? [ስለዚህ ለበለጠ **ቁ.6** ይመልከቱ።]
- ጋዜጠኞች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ሰለባ የሆኑ ሰዎች ጋር ስለሚያደርጉት ውይይት ህጋዊ ችግሮች እምብዛም አያስቡም። ምንጫችሁ በፍርድ ቤት ፍትህ ለመፈለግ አላማ ያላቸው ከሆነ፣ ከጋዜጠኞች ጋር መነጋገር ጉዳያቸውን ሊያበላሽ ይችላል። እንዲሁም ሁሉም ሰነዶችዎ ሊገኙ የሚችሉ ማስረጃዎች እንደሆኑ ሊቆጠሩ እንደሚችሉ ማወቅ አለብዎት።

© Dart Centre Europe

## የፍትህ ሂደቱ እና የበርካታ መግለጫዎች አደጋ

ለጥቃት ሰለባዎች ፍትህን የመፈለግ ህጋዊ ሂደት አንዳንድ ጊዜ በበርካታ ቃለመጠይቆች ሊጣስ ይችላል። ኮሎምቢያዊቷ ጋዜጠኛ ጂነት ቤዶያ ሊማ እንደሚከተለው ትገልጸዋለች፦

> በጾታዊ ጥቃት ወቅት ከሚገጥሙን ችግሮች አንዱ ነው።
>
> በኮሎምቢያ ተጎጂዋ ስለ ክስተቶቹ ምስክርነት ከአንድ ጊዜ በላይ የመስጠት ግዴታ እንደሌለባት ህጉ ይናገራል። ነገር ግን ከሞላ ጎደል ሁሉም ተጎጂዎች ስለአንድ አጋጣሚ ከአራት በላይ ምስክርነት እንዲሰጡ ይገደዳሉ እና ይህ በግልጽ የታሪኮች አለመመጣጠን ያስከትላል፤ ይህም ብዙውን ጊዜ የፍትህ ሂደቶች መበላሸት ያስከትላል፣ ተጎጂዋ ለመገናኛ ብዙሃን ምስክርነቷን ስትሰጥ የበለጠ ይባባሳል።
>
> እንደ አለመታደል ሆኖ ጋዜጠኞች 'እውነተኛውን' ታሪክ ለማግኘት በምስክሮቹ አለመጣጣም ላይ ይደገፋሉ፤ ነገር ግን ይህ የሚያመነጨው የሂደቶቹ መዘጋት ነው።
>
> በተመሳሳይም ፍርድ ያልተሰጠው የወሲብ ጥቃት የወንጀል ድርጊት የመከላከያ ክርክሮችን ወደ ወንጀለኞቹ እንዲያቀርቡ ያደርጓቸዋል፤ እነዚህም ማስረጃዎቻቸውን በብዙ አጋጣሚዎች ተጎጂዎቹ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በሚያደርጉት በቃለ መጠይቅ መካከል በሚፈጥሩት 'ተቃርኖ' ላይ ይመሰረታሉ። ዳኞች የተጎጂው ምስክርነት በካሜራ ፊት የሚቀርብበትን መንገድ፣ ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ በጭራሽ አያስቡም። እናም በታሪኩ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ከአንድ ጋዜጠኛ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ከሰነ-ልቦና ባለሙያ ወይም ከጤና ባለሙያ የተለየ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ለጥናታችን አስተዋጽኦ ያደረገችው ጂነት ቤዶያ ሊማ በግንቦት 2000 እና በነሐሴ 2003 በኮሎምቢያ ሁለት ጊዜ ታፍናለች። እ.ኤ.አ. በ 2001 **የዓለም አቀፍ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን** በጋዜጠኝነት የጀግንነት ሽልማት አግኝታለች።በ2020 ከአለም **የጋዜጦች እና የዜና አታሚዎች ማህበር** የነፃነት ወርቃማ ብዕር ሽልማት አሸንፋለች።

## ተጨማሪ መረጃዎች፡ የፈቃድ ስምምነት

በምስራቅ አፍሪካ የምትኖር አሜሪካዊት ጋዜጠኛ ጂና ሙር ለዚህ ምክክር አበርክታለች።

በእነዚህ ሁለት ጠቃሚ ጽሑፎች ውስጥ የስምምነት ጉዳዮችን በበለጠ ዝርዝር ትዳስሳለች: **The Pornography Trap in Columbia Journalism Review** እና **Five Ideas on Meaningful Consent in Trauma Journalism**.

ይህንን ጽሑፍ ያጋሩ

እባክዎን በግራጫ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

# #4.

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ አሰራሮች

# ተጎጂዎች በራሳቸው መንገድ እና በራሳቸው ጊዜ እንዲናገሩ ፍቀድላቸው

© Dart Centre Europe

# #4.

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ አሰራሮች

## ተጎጂዎች በራሳቸው መንገድ እና በራሳቸው ጊዜ እንዲናገሩ ፍቀድላቸው

በወሲባዊ ጥቃት ጊዜ ሰዎች በአጥቂዎች እንደ ዕቃ ይቆጠራሉ - በሚደርስባቸው ነገር ላይ ቁጥጥር እንዳላቸው ግለሰቦች አይደሉም የሚቆጠሩት። ያንን ሁኔታ በመለወጥ ተጠያቂዎችን ታሪካቸውን እንዴት እንደሚናገሩ የመወሰን ዕድል መስጠት ይችላሉ?

**ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎችን ግምት መስጠት፣ በአክብሮት የመያዝ እና ክብራቸውን የመጠበቅ አስፈላጊነት የታወቀ መሆን አለበት። ነገር ግን ይህ በተግባር ላይ ምን ያካትታል?**

**እንደ ጋዜጠኛ ተጎጂዎችን ቃለ መጠይቅ ሲያደርጉ፣ እርሰዎ ላቅ ያለ ቦታ ላይ ነዎት - ምንም ባይሰማውም እንኳ።መተማመን እና የስሜት ደህንነት ልብ ማለት የሚያስፈልጉዋቸው ጉዳዮች ይሆናሉ። ታድያ፣ በጥቂቱም ቢሆን እንደ መቸኮል ወይም ምላሽ እንዲሰጡ መግፋት የመሰሉ ዋናውን በደል የሚያስተጋባ ምንም ነገር አለማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። በአደገኛ ቦታ ላይ እና የጊዜ ገደብ በሚጨናነቁበት ወቅት ላይ ሲሆኑ ይህ በቀላሉ ከግምት ውጭ ሊሆን ይችላል።**

**ለውይይቱ በቂ ጊዜ ለማቀድ ቅድሚያ ይሰጡ እና ተጠያቂውን ማወቃቸው ያረጋግጡ፡-**

- **ደስ የማይላቸውን ማንኛውንም ጥያቄዎች መመለስ አያስፈልግም።**
- **በማንኛውም ጊዜ ማቆም ምንም ችግር የለውም።**
- **እንዳይታተም የሚጠይቁዋትን ማንኛውንም ዝርዝር ማክበር አለብዎት።**

**በመጀመሪያ ተጠያቂውን እንደ ሰው ይመልከቱ - በሁለተኛ ደረጃ ነው ታሪኩ ለመሰነድ እንደምንጭ መታየት ያለባቸው።**

የሚዲያ ቃለ መጠይቅ በዝባዥ ወይም ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ ከተፈጸመ ተጎጂዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ይህ ክፍል አሰቃቂነትን የተገነዘበ ቃለ መጠይቅ ውስጥ ያሉ መሰረታዊ ነገሮችን ያብራራል፤ የሚቀጥለው [**ቁ.5**] የተወሰኑ የስሜት-ቀውስነት ምላሾችን እና ከተጎጂዎች ጋር በሚሰሩበት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ተግዳሮቶች በበለጠ ዝርዝር ይመለከታል።

ብዙ ጊዜ ጋዜጠኞች፣ እንደ ጾታዊ ጥቃት ወይም ማሰቃየት የመሰሉ አስደንጋጭ እና አሳማሚ ታሪኮችን ማውራት ብቻ ስለባውን ሊጎዳ እንደሚችል መጨነቃቸው የሚገርም አይደለም። ባይነገሩ የሚሻሉ ነገሮችን እንደገና እያነሱ ነው ብለው ይፈሩ ይሆናል። ወይም እንደ ሰው ታሪካቸውን ሲናገሩ የሚያጋጥመውን ጭንቀት አዲስ ጉዳት ከማድረስ ጋር ያመሳስሉት ይሆናል።

ከፆታዊ ጥቃት ተጎጂዎ ጋር የሚሰሩ አብዛኛዎቹ የስሜት-ቀውስን ለባለሞያዎች መናገር ራሱ ትልቅ አደጋዎች ያሉበት እንደሆነ አያስቡም። ቃለ-መጠይቅ የሚደረግለት ሰው በንግግሩ ወቅት ምን ያህል ደህንነት እንደሚሰማው፣ ስለሚያወራው ምን ያህል እንደሚቆጣጠሩ እና እንዲሁም ታሪካቸው በኋላ እንዴት እንደሚታተም በሚሉ ጥያቄዎች ስለሚመረኮዝ ነው[**ቁ.7** እና **ቁ.8** ይመልከቱ]። ሰዎች እንደተፈረደባቸው ሲሰማቸው ወይም እንዳልሰሙ ሲሰማቸው ወይም ላልሆነ ዓላማ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ሲሰማቸው፣ ጉዳቱ ሊከሰት ይችላል። በአሰቃቂነት ዙርያ በሚደረጉ ቃለመጠይቆች ውስጥ፣ መተማመን ሰስ እና በቀላሉ የሚበላሽ ነገር ነው።

ማውራት በራሱ ከመዘዝ ነፃ ነው ከሚለው ሀሳብ የሚቃረኑ ልዩ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው ከዚህ በፊት የሸሸገው እና ከዚህ በፊት ያልተመረመረ ከባድ አሰቃቂ ነገር ካጋጠመው፣ ለምሳሌ በልጆች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት፣ መናገር በራሱ አለመረጋጋትን ሊፈጥር እና የተለያዩ አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል። በአጠቃላይ ያልተጠበቁ መረጃዎችን ከማቅረብ ይጠንቀቁ።

© Dart Centre Europe

## ሂደቱን እንዴት ከብዝበዛ ይልቅ የትብብር ማድረግ እንደሚቻል

ለተጎጂዎች ፆታዊ ጥቃት እንደ መሠረታዊ የቁጥጥር መጥፋት ነው – የሆነ የደረሰባቸውን ነገር ለመከላከል አቅመ ቢስ የሆነባቸው። ይህንን ለመቃወም አንዱ መንገድ እንደ ጋዜጠኛ ያለዎትን አንዳንድ የመቆጣጠር ኃይል መስጠት እና በሂደቱ ላይ በሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ እንደሚሳተፉ ማድረግ ነው። ትናንሽ ምርጫዎች እንኳን ትልቅ ለውጥ ያመጣሉ።

በውይይት ውስጥ ማንኛውንም ዝርዝር ከመግባትዎ በፊት የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡-

- መናገር ከባድ ሊሆን እንደሚችል ይግለጹላቸው።
- የት ቃለ መጠይቅ እንዲሚደረግላቸው እንደሚፈልጉ ለመወሰን ሙሉ ለሙሉ ያሳትፏቸው።
- ለንግግሩ ብዙ ጉልበት የሚኖራቸው መቼ እና ለምን ያህል ጊዜ ማውራት እንደሚፈልጉ – የትኛው ሰዓት እንደሚስማማቸው ይጠይቁ?
- በክፍሉ ውስጥ ከእነሱ ጋር መሆን የሚፈልጓቸው እንደ ጓደኛ ወይም ዘመድ ያለ ሰው ካለ ይጠይቁ።
- ሊናገሩበት የማይፈልጉት ነገር ካለ ጠይቋቸው።
- ደስ የማይላቸው ማንኛውንም ነገር መመለስ እንደሌለባቸው አረጋግጡላቸው።

ወደ ንግግሩ ከመግባትዎ በፊት እንደ ቃለ-መጠይቅ አድራጊ፣ ሰዎችን ለረዥም ግዜ መናገራቸው እና እረፍት እንደሚያስፈልጋቸው እንዴት እንደሚገነዘቡ ከወዲሁ ማስረዳት ጥሩ ነው። ሰዎች ታሪካቸውን በሚናገሩበት በመሃል ከመጠን በላይ ሊገቡ ይችላሉ። እና በተጨማሪ፣ አብዛኞቻችን ጥያቄዎችን የሚጠይቅን ሰው ለማስደሰት፣ ለመቀጠል ከፍተኛ ፍላጎት ያጋጥመናል። ሲደክማቸው ወይም ውይይቱ ወደ ደስ የማይላቸው አቅጣጫ በሚሄድበት እና ከአቅማቸው በላይ እንደተናገሩ ምልክት ላያሳዩ ይችላሉ። ቃለ መጠይቁ ከመድረሱ በፊት ይህንን ማንሳት – እና ምናልባት በአንድ የተወሰነ ምልክት ላይ መስማማት – እረፍቶችን የሚጠቁሙ ወይም አቅጣጫው ወደ ደህንነቱ የተጠበቀ ርዕሰ መቀየር የበለጠ ቀላልና እና ብዙም የማይረብሽ ያደርገዋል።

## በሚጠቀሙባቸው ቃላት ላይ መስማማት

ክፍል **ቁ.7** በሚታተምበት ጊዜ ስለቋንቋ ምርጫዎች የበለጠ ይናገራል። በቃለ መጠይቁ ወቅት፣ ተጎጂውን የሚስማማቸውን ቃላት እየተጠቀሙ መሆንዎን ያረጋግጡ። የአካባቢ ፈሊጦች እዚህ ጠቃሚ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ። አንዳንድ ግልጽ ደንቦች አሉ። ለምሳሌ ወንጀለኛን እንደ የተጎጂውን ፍቅረኛ መግለጽ ፈጽሞ ተገቢ አይደለም።

አብዛኛዎቹ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች እራሳቸውን እንደ 'ተጎጂዎች' ይገልጻሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶች 'ሰለባ' የበለጠ ትክክለኛ ቃል እንደሆነ ሊሰማቸው ይችላል እና ሌሎች ደግሞ ሁለቱንም ለማስወገድ ይፈልጉ ይሆናል።በየትኞቹ ቃላቶች ላይ ጥርጣሬ ካለዎት፣ ከጠያቂዋ ጋር ያረጋግጡ እና ምን እንደሚመርጡ ይጠይቁ። በአጠቃላይ፣ ሰዎች እራሳቸውን እንዴት እንደሚለዩ ማክበር ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው።

## የመስማት ችሎታ

ሰዎች እንደተሰሙ ሲያምኑ፣ የበለጠ የደህንነት ስሜት ይሰማቸዋል እና ከዚያም ሃሳባቸውን በብቃት መሰብሰብ ይችላሉ። በደንብ ማዳመጥ እንደሚቻል ማወቅ ጋዜጠኛ ተጎጂዎች ወደ ውይይት ለማምጣት የሚያስፈልገው ብቸኛው በጣም አስፈላጊ ክህሎት ነው። ለርዕስ ጉዳይ ቦታ መስጠት እና ቀላል እና በአንጻራዊነት ክፍት የሆኑ፣ ሰዎችን እንዴት እንደሚመልሱ ምርጫ የሚሰጡ ጥያቄዎችን መጠየቅን ይጨምራል። ምርጫው ግን ከመጠን በላይ እንዳይሆን ይመረጣል።

ያስታውሱ፣ በክፍል **ቁ.2** እንደተብራራው፣ ፈቃድን ማረጋገጥ ቀጣይ ሂደት እንጂ የአንድ ጊዜ ክስተት አይደለም።ጥያቄውን ከማቅረብዎ በፊት፣ "ስለ… (አንድ የተወሰነ ርዕሰ ወይም ክስተት) ብጠይቅዎት ችግር አለው?" በማለት ሊጠይቁት ይችላሉ። ከዚያ ሰዎች በነፃነት ምላሽ እንዲሰጡ ይፍቀዱ። በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና ሌሎች ቦታዎች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ተጎጂዎች ጋር የምትሰራው ኬቲ ሮብጃንት ለጋዜጠኞች ልዩ የሆነ ምክር አላት፡-

> ስለ አጠቃላይ ክስተቶች ክፍት የሆኑ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይልቅ፣ ምንጩን ሊናገሩት የሚፈልጉትን ልዩ ነገር እንዳለ አስቀድመው ይግለጹ። ከዚያ ስለዚያ ክስተት ወይም ርዕሰ የቻሉትን ያህል እንዲነግሩዎት ይጠይቋቸው። ለማጋራት ምቾት የሚሰማቸውን ሁሉንም መረጃዎች ከሰጡዎት በኋላ ጉልህ የሆኑትን ክፍሎች ማውጣት የእርስዎ ስራ ይሆናል። ይህ ማጋራት ወይም ማሰብ የማይፈልጉትን ዝርዝሮች እንዲናገር ማስገደድን ማስወገድ የሚቻልበት አንዱ መንገድ ነው።[ሀ]

ሀ. ይመልከቱ፡ https://dartcenter.org/resources/reporting-refugees-tips-covering-crisis reporting-refugees-tips-covering-crisis

የውጤታማ ማዳመጥ ጠቋሚዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ዝምታን መፍቀድ እና ሰዎች ሀሳባቸውን እንዲሰበስቡ ቦታ መስጠት።
- እየተከታተሉ መሆንዎን ለማሳየት በቃልም ወይም፣ እየቀረጹ ከሆነ፣ የቃል ያልሆኑ ምልክቶችን ይጠቀሙ።
- ቁልፍ ነጥቦችን መረዳትዎን ለማረጋገጥ ተመልሰው መፈተሽ።
- ከተናጋሪው ትኩረትን እንዳይወስዱ ከራስዎ ምቾት ማጣት ጋር እንዴት በትዕግስት ቁጭ ማለት እንደሚችሉ ማወቅ።

እነዚህን ማስወገድ ይሞክሩ፡-

- የሰዎችን ዓረፍተ ነገር ለእነሱ መጨረስ ወይም የሃሳባቸውን ሰንሰለት በድንገት መቁረጥ (በማስታወስ ውስጥ ካልጠፉ በስተቀር – ክፍል **ቁ.5** ይመልከቱ)።
- ማንኛውንም የፍርድ ስሜት መስጠት – ለምሳሌ፣ አንድ ሰው የሚያስደነግጥ ነገር ሲያወራ የተደናገጠ ፊት ማሳየት (ምን ያህል እንዳሳሰባቸው ወይም እንዳዘኑ መግለጽ ደህና ነው።)
- ማንኛውም ተገቢ ያልሆነ አካላዊ ዝርዝሮች ለማግኘት ግፊት ማድረግ።
- ለሰዎች ምን እንደሚሰማቸው እንደሚያውቁ መንገር (ሰዎች እርሰዎን ማመን አይችሉም)።

እንዲሁም ተመሳሳይ ክስተቶች እንዳጋጠሙዎት ለሰዎች በመንገር ወይም ወደ የግል ታሪክ ዝርዝር ውስጥ ላለመግባት መጠንቀቅ አለብዎት።

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ይህ መተማመንን ሊፈጥር እና ውይይቱን ሊያዳብር ይችላል፣ በሌሎች ውስጥ፣ ከተናጋው ትኩረቱን ሊወስድ ይችላል እና ለእነርሱ ያጋጠማቸው ተሞክሮ እየቀነሱ ወይም ወደ ጎን እየገፉ እንደሆነ እንዲሰማቸው ያደርጋል። (ጤናማ ወሰንን የመጠበቅ አስፈላጊነት በክፍል **ቁ.6** የበለጠ ተብራርቷል።)

## ጊዜን መቆጣጠር እና በጥሩ ሁኔታ ማብቃት

የዚህ ክፍል ርዕስ፣ **ተጎጂዎችን በራሳቸው መንገድ እና በራሳቸው ጊዜ እንዲናገሩ ቦታ መፍቀድ ማለት ግን ጊዜን በመቆጣጠር ረገድ** ሙሉ በሙሉ ቸልተኛ መሆን አለብዎት ማለት አይደለም። ሰዎች ለአደጋ የተጋለጡ ሲሆኑ ውይይቱ አንዳንድ መመሪያዎችን ቢኖራቸው ይጠቀማሉ። እንዲሁም ከላይ እንደተጠቀሰው የተጽዕኖ ደረጃቸውን መከታተል ያስፈልግዎታል። (በአካባቢው ውስጥ የሚቆዩ ከሆነ፣ ሁል ጊዜ ተመልሰው መጥተው ውይይቱን ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ።)

አንዳንድ የሕክምና ባለሙያዎች ስለ 'ሦስት ሦስተኛው' ደንብ ይናገራሉ።

በሐሳብ ደረጃ የውይይቱ የመጀመሪያ አንድ ሦስተኛው ተናሪው በአንፃራዊነት ደህንነቱ በተሰማው ጊዜ እና ልምዶች ላይ ማተኮር አለበት። መካከለኛው ክፍል፣ ለምሳሌ አሰደንጋጭ ክስተቶች፣ በጣም አስቸጋሪ በሆነው ነገሮች ላይ ያተኩራል። የመጨረሻው ክፍል ደግሞ፣ በአሁን እና በወደፊቱ ላይ – ተጎጂውን ወደ እዚህ እና አሁን እንዲመለስ እንደ ድልድይ የሚረዳ ማንኛውም ነገር ይሆናል። ግለሰቡን በቃለ መጠይቁ መጨረሻ ላይ በደረሰበት በጣም መጥፎ ነገር ውስጥ ተዘፍቆ መተው የለብዎትም።

በአዎንታዊ ሁኔታ ለመጨረስ ይሞክሩ፤ ነገር ግን ከመጠን በላይ አያድርጉት፣ እንዲሁም ነገሮች ከእውነታው የተሻሉ እንደሆኑ ያስመስሉ። ሰዎች ይህን ለመቋቋም ምን ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኙት እና ለሌሎች ምን እንደሚመክሩ መጠየቅ ይችላሉ። ጠንካራ የመጨረሻ ነጥብ ማግኘት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። ቢያንስ ሰዎች በቀሪው የቀኑ ሰዓት ምን እንደሚያደርጉ ሁልጊዜ መጠየቅ ይችላሉ። እርግጥ ነው፣ ሰዎችን ማመስገን አይርሱ፣ እና ከወደፊቱ ግንኙነት፣ ስለ ጽሑፉ መረጃ በመላክ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች የገቡትን ማንኛውንም ቃል ይጠብቁ።

ይህንን ጽሑፍ ያጋሩ

እባክዎን በግራጫ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ እስራሮች

# #5.

# አስቃቂነት በትውስታና እና የደህንነት ስሜት ላይ ያለው የማያቋርጥ ተጽእኖ ይረዱ

# #5.

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ አሰራሮች

# አስቃቂነት በትውስታና እና የደህንነት ስሜት ላይ ያለው የማያቋርጥ ተጽእኖ ይረዱ

ከአስቃቂነትን የተያያዙ ምላሾች አንዳንድ መሰረታዊ እውቀት መኖር ፈታኝ የሆኑ የቃለ መጠይቅ ሁኔታዎችን ለመወጣት እና መዘዝ የሚያስከትሉትን የዘገባ ስህተቶችን ለማስወገድ ይረዳዎታል።

አሰጨናቂ ክስተቶችን እንደገና ሲጎበኙ ሰዎች ሊበሳጩ ይችላሉ። ጭንቀት በራሱ ሰዎች ለመናገር ጥሩ ቦታ ላይ አይደሉም ማለት አይደለም። ነገር ግን አንዳንድ ምላሾች ሰዎች በንግግሩ ውስጥ ደህንነት እንደማይሰማቸው ሊያመለክቱ ይችላሉ። ሊያቋርጡ፣ በሩን ለማግኘት ሊያፈላልጉ ወይም በጥቃቱ ጊዜ ያጋጠማቸው ዓይነት አካላዊ ግብረመልስ ሊያሳዩ ይችላሉ።

የስሜት ቀውስ ውስብስብ የባዮ-ሳይኮ-ማህበራዊ ልምድ ነው፤ ጭንቀት በጭራሽ አንድ ነገር ብቻ አይደለም - የተለያዩ ክፍሎች ድብልቅ ነው። የሚዲያ ባለሙያ እንደመሆንዎ መጠን የአዕምሮ ሳይንስን ማወቅ አያስፈልገዎትም ነገር ግን አንዳንድ መሰረታዊ፣ የመግቢያ ግንዛቤ መኖር የተሻሉ ውሳኔዎችን ለማድረግ ይረዳዎታል፦

- ቃለ መጠይቅ የተደረገለት ሰው በምን ሁኔታ እንዳለ እና መቼ ከማውራት እረፍት ሊያስፈልገው እንደሚችል።
- እንደ ጥፋተኝነት እና እፍረት ባሉት አስቸጋሪ ስሜቶች ላይ ነዳጅ እንዲጨምሩ የሚያደርግ መርማሪ የሚያስመስልዎት የጥያቄ ዘይቤዎችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል።
- እስከምን ድረስ አንድ ሰው ስለ አንድ አሰደንጋጭ ክስተት ያለው ትውስታ ትክክለኛነት እና ለምን በእነርሱ የትውስታ ክፍተት ውስጥ ማስገባት እንደሌለብዎት ላይ መታመን ምክንያታዊ ነው።

አሰገድዶ መድፈር ማንኛውም ሰው ሊደርስበት ከሚችለው እጅግ በጣም አስቃቂ ገጠመኞች አንዱ ነው። ተጎጂዎች ላጋጠማቸው ቃላት ለማግኘት የሚቸገሩባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ።

ታሪካቸው የሰሙ ሌሎች ሰዎች ምን ይላሉ በማለት የሚከሰት ማፈር እና መፍራት የሰዎችን የንግግር ችሎታ ለመዝጋት ትልቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ፣ ስለአስቃቂ ሁኔታ ማውራት ሰዎች ለመናገር በጣም የሚያሀቀዩ እና የሚያደክሙ ስሜቶችን ሊያመጣ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ዝምታ ጥሩ ምላሽ ነው። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የነገሮችን ቃላቶች የሰው ልጅ የማስታወስ ችሎታ በአስቃቂ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ጋር በተገናኘ ለተለየ ምክንያት ከባድ ሊሆን ይችላል።

ጥቃት ሲደርስብን ወደ የመዳን ሁኔታ እንሄዳለን። ትውስታዎች አሁንም ተመዝግበዋል – ብዙ ጊዜ ግልፅ ባለ መልኩ – ነገር ግን አእምሮው በተለምዶ በሚያስማራቸው የሰርዓት መርሆዎች መሰረት አጣርቶ አያስወግዳቸውም (ይልቁንም ለበለጠ መሰረታዊ የመዳን ሰርዓቶች ቅድሚያ ይሰጣል)። ወሲባዊ ጥቃት በደረሰባቸው ሰዎች የተቆራረጠ እና የተበታተነ የማስታወስ ችግር መኖሩ የተለመደ ነው። በጊዜ ቅደም ተከተል ላይ ግንዛቤ የመስጠት ችግር ያለባቸው ክፍተቶች ወይም አለመጣጣሞች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንድ ነገሮች በልዩ ኃይል ሊመለሱ ይችላሉ፤ ሌሎች ባዶ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም በመጀመሪያ በትውስታ ውስጥ ያልተቀመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። [ሀ]

ሀ. ጾታዊ ጥቃት በደረሰባቸው ሰዎች የማስታወስ ችሎታ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ጠቃሚ መግቢያ ለማግኘት **G. Smith and S. Heke፣ 'From Report to Court: Psychology፣ Trauma and the Law' (2010)**፣ ይመልከቱ እዚህ አለ**'From Report to Court: Psychology, Trauma and the Law' (2010)**፣ ይመልከቱ እዚህ አለ

ለእርስዎ እንደ ጋዜጠኛ በተግባራዊ መልኩ ይህ ማለት፡-

- ተጎጂው ስለአጋጠመው ነገር ፍጹም ወጥነት ያለው ወይም ምክንያታዊ ዘገባ እንዲሰጥዎ መጠበቅ የለብዎትም። አለመመጣጠን የማታለል ዓላማን የሚያሳይ ማስረጃ አይደለም።
- የእርስዎ ምንጭ ማናቸውንም የታሪኩን ልዩነቶችን ያጸዳሉ ብሎ መጠበቅ ፍትሃዊ አይደለም – ላይችሉ ስለሚችሉ። ትክክለኛ ቅድመ-ተከተሉ አስፈላጊ ከሆነ፣ ሌሎች ክስተቶችን የሚያረጋግጡ መንገዶችን ይፈልጉ።
- ወደ ኋላ መዞር እና ቀላል የማብራሪያ ጥያቄ መጠየቅ ቀለል ባለ መንገድ ከቀረበ ጥሩ ነው። ነገር ግን በአንድ ሰው ትውስታ ውስጥ ክፍተት ወይም እንቅፋት ካጋጠመዎ በግፊት መረጃ ለማግኘት አይሞክሩ። ያ ከአቅም በላይ በሆነ መንገድ አንድ ነገር ሊያጎድል ይችላል [ከዚህ በታች ያለውን ሣጥን ተመልከት]።
- አብረዋቸው እየሰሩ ያሉ ሌሎች ሰዎች – ለምሳሌ አዘጋጆችና አራሚዎች – እነዚህን ገደቦችም ማወቅ አለባቸው።

---

# ለጭንቀት ምላሽ መስጠት

ጭንቀት እኛ በምንጠብቀው መንገድ አይታይም። ስሜታዊ ያልሆኑ የሚመስሉ እና በጣም አስከፊ ስለሆኑት ነገሮች ወጥ በሆነ ድምጽ የሚያወሩ ሰዎችን ወይም በማይሆን ቦታዎች ላይ በመሳቅ ውጥረትን የሚለቁ ወይም ትንሽ ወጣ ያሉ የሚመስልዎት ሊያጋጥሙዎት ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ተፈጥሮአዊ፣ በደንብ የተመዘገቡ ግለሰቦች ከአሰቃቂ ሁኔታ በኋላ የሚናራቸው የሚያሳዩት ምላሽ ነው። የሚያገኟቸውን እያንዳንዱን ሰው በክፍት አእምሮ ይያዙ እና ትክክለኛ የመልስ አሰጣጥ መንገድ አለ ብለው እንዳያስቡ ይጠንቀቁ።

ሰዎች ስላለፈው ነገር ሲናገሩ፣ በተጠቁባቸው ጊዜ (ወይም ጊዜያት) የነበራቸውን ተመሳሳይ ስሜቶች እና አካላዊ ትውስታ እንደገና ሊሰማቸው ይችላል። ይህ መሰስተኛ እና በቀላሉ የማይታወቅ ወይም ከባድ በመሆኑ የተነሳ ሰዎችን ከአሁን በኋላ እነዚያን ስሜቶች እንዲታገሡ ከአቅማቸው በላይ የሚገፋ ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው ጠንከር ያለ ምላሽ ካሳየ – ለምሳሌ በከፍተኛ ሁኔታ ይናደዳል፣ ማልቀስ ይጀምራል ወዘተ – ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ከመቸኮልዎ በፊት ነገሮችን በራስዎ ውሳኔ ቀነስ ያድርጉ። ካሜራውን በችኮላ ማጥፋት ወይም ቃለ መጠይቁን ማቋረጥ አንድን ሰው እንደዚህ አይነት ስሜት መኖሩ ስህተት እንደሆነ በመግለጽ ሳያስበው ሊያሳፍር ይችላል። አካላዊ ንክኪን ስለመጠቀም ይጠንቀቁ። ያ በተለይ ያልተጠበቀ ከሆነ አስጊ እና አለመረጋጋትን ሊያስከትል ይችላል። በምትኩ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- የመረጋጋት ማሳያ መፍጠር
- የሆነውን ነገር በእነርሱ ላይ መድረሱ እንደሚያሳዝንዎት ይግለጹላቸው።
- እዚህ ክፍል ሰዎች ከእርስዎ ጋር ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ያስታውሷቸው – አሁን እየሆነ እንዳልሆነ ያረጋግጡላቸው።
- በዚህ ጊዜ ምን ሊረዳቸው እንደሚችል ጠይቃቸው። ከቃለ መጠይቁ እረፍት ይፈልጋሉ? ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ስሜት ሲሰማቸው ምን ያደርጋሉ?

## አንድ ሰው በትዝታ ውስጥ ሲጠፋ

በአእምሮ መረቅ በወሲባዊ ጥቃት ጊዜ የሚገለጽ የተለመደ የመዳን ምላሽ ነው። ሁኔታው አስጨናቂ ሲሆን እና ምንም እውነተኛ የማምለጫ መንገድ ከሌለ አንጎል በድንገት ቅጽበታዊ ጥሪ በማድረግ ነገሮችን ለመዝጋት እና ጥቃቱ በትክክል እንዳልተከሰተ አስመስሎ እንዲለይ ያስችለዋል።

ስለደረሰባቸው እንደገና መናገር ሰዎች ጥቃቱ መልሶ እየተከሰተ እንደሆነ እንዲሰማቸው ሊያደርግ ይችላል። አንድ ሰው የደህንነት ስሜት ሲሰማው እና በአእምሮው ሲረቅ ማወቅ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። ሆኖም ግን ሰዎች የሚከተሉትን ሊጀምሩ ይችላሉ፡-

- ትኩረትን ማጣት፣ እንቅልፍ የያዛቸው ይመስላሉ ወይም ለጥያቄዎች መልስ መስጠት ያቆማሉ።
- ስለ ሙቀት ስሜት ቅሬታ ማሰማት ወይም በድንገት መላብ ይጀምራሉ።
- ስለ ራስ ምታት ወይም የአካል ህመም ቅሬታ ማሰማት።
- ለመውጣት ክፍሉን መቃኘት።

© Dart Centre Europe

በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና ሌሎች ቦታዎች ከስደተኞች እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ከደረሰባቸው ተጎጂዎች ጋር የምትሰራው ኬቲ ሮብጃንት ይህ ከተፈጠረ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለጋዜጠኞች ይህንን ምክር ትሰጣለች፡-

> ተግባሮችዎን ሊገመቱ የሚችሉ ያድርጓቸው …ምንጊዜም ፈቃድ መጠየቅ ወይም ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለግለሰቡ ማሳወቅ ጥሩ ነው። በጣም ጥሩው ነገር እነሱን ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመቀየር በፍጥነት መሞከር ነው። ንግግርዎን ይቀጥሉ። ስለ እዚህ እና አሁን ያሉ ነገሮችን ይጠይቁ፣ ለምሳሌ፣ “የት እንዳለህ ልትነግረኝ ትችላለህ? ክፍሉ ምን እንደሚመስል መግለፅ ትችላለህ? እነዚያ አይነት ጥያቄዎች እንደ “ደህና ነህ?” ከመሳሰሉት አጠቃላይ ጥያቄዎች የበለጠ አጋዥ ይሆናሉ። [ለ]

## እፍረት እና እምነት

ስለ ወሲባዊ ጥቃት በሚደረግ ንግግር ውስጥ ለጠንካራ የኀፍረት እና የጥፋተኝነት ስሜት እንዲፈጠር ምን ያህል ቀላል እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህ በድንገት ሊከሰት እና በማንኛውም ጊዜ ከየንግግር ርእሱ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ መስሎ ሊታይ ይችላል። ሰዎች ለደረሱባቸውና ጥፋታቸው ሊሆን በማይችሉ ነገሮች ራሳቸውን መወንጀል ያልተለመደ ነገር አይደለም።

እና ይህ ስለ ጾታዊ ጥቃት ስነ ልቦና ብቻ አይደለም – የተደፈሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከማያምኑዋቸው፡ የደረሰባቸውን ዝቅ ከሚያደርጉ ወይም ራሳቸው ጥፋተኛ እንደሆኑ ከወነጀሏቸው ቤተሰብ እና የማህበረሰቡ አባላት ጋር መታገል ይኖርባቸዋል።

ስለዚህ ጉዳተኛው እንደማታምኑ ወይም በእነሱ ላይ ለደረሰው ነገር በማንኛውም መንገድ ተጠያቂ እንደሆኑ የሚጠቁም ማንኛውንም ቋንቋ ከመጠቀም ይጠንቀቁ። በዚህ ምክንያት፣ “ለምን” የሚሉ ጥያቄዎች አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። መርማሪዎች ይወዷቸዋል ምክንያቱም ለመመለስ አስቸጋሪ ስለሆኑ እና የጥፋተኛ እንደምታ ስለሚያሳዩ። ለምሳሌ፣ አንድን ሰው፣ “በዚያን ጊዜ ለምን እዚያ ነበርክ?” ብሎ መጠየቅ፣ መጀመሪያ ላይ እዚያ መሆን እንደሌለባቸው ያስመስላል።

ስለ ስሜቶች መረጃ የሚሹ ጥያቄዎች፣ ለምሳሌ “…ሲያደርጉ ምን ተሰማዎት?” ለተወሳሰቡ እና ተለዋዋጭ ስሜቶች ሊያድሱ እና ነዳጅ ሊጨምሩ ስለሚችሉ በተቻለ ሁኔታ መወገድ አለባቸው።

እና ቀደም ሲል እንደተብራራው፣ ስለተፈጠረው ነገር ተገቢ ያልሆኑ ወይም አካላዊ ዝርዝሮች ላይ የሚያተኩሩ መርማሪ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይቆጠቡ።

ተጎጂው እውነት እንዳልሆነ በምታውቀው ነገር ካመነ ወይም ያለመስማማት ቢፈጠር እና እነሱን መገዳደር ከፈለግክ ይህን ለማድረግ ትክክለኛው ሰው እንደሆኑ እና ምን ጥቅም እንደሚያስገኝ ራስዎን ይጠይቁ። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመቀበል ከአቅማቸው በላይ የሆነ የደረሱባቸውን ነገሮች አንዱ ለመከላከል ሲሉ አንዳንድ እምነቶችን ሊደገፉ ይችላሉ።

ይህንን
ጽሑፍ ያጋሩ

ለ. ይመልከቱ፡ https://dartcenter.org/resources/reporting-refugees-tips-covering-crisis.

እባክዎን
በግራጫ መደብ ላይ
የሰፈረውን ጽሑፍ
ብቻ ያትሙ

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ አሰራሮች

# የእራስዎ ስሜታዊ ደህንነት እንዴት የዚሁ አካል እንደሆነ ይረዱ

# #6.

© Dart Centre Europe

አደጋን የማያስከትሉ ሦስት አስፈላጊ አሰራሮች

# የእራስዎ ስሜታዊ ደህንነት እንዴት የዚሁ አካል እንደሆነ ይረዱ

# #6.

ለጭካኔ መጋለጥ በሚዲያ ባለሙያዎች ላይ ስሜታዊ ጫና ይፈጥራል። እራስዎን መንከባከብ ለራስዎ - እና ለምንጮችዎ ያለዎት ግዴታ ነው።

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) መሸፈን ስሜትን የሚያደክም ስራ ነው፣ ይህም በአደገኛ እና ባልተረጋጉ አካባቢዎች ለሚሰሩ የሚዲያ ባለሙያዎች የግል አደጋዎችን ያስከትላል። የእራስዎን ጭንቀት ችላ ለማለት ሊያዳሉ ይችላሉ፣ ምክንያቱም ደግሞ መጠኑ ተጎጂዎችን እያጋጠሟቸው ካሉት ጋር ሲነጻጸር ትንሽ እንደሆነ ስለሚሰማዎ ነው። ቢሆንም፣ እነዚያ ትናንሽ ተጽእኖዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊጨመሩ እና የበለጠ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይገነዘቡ፤ ይህም ከስራ ባልደረቦችዎ እና ከአደጋ ከተጎጂዎች በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።**

**ለአንድ ተጋላጭ ምንጭ ለወደፊት የማይጠበቁ ስሜታዊ ወይም የተግባር ድጋፍ እንዲሰጡ መገፋት፣ አንድ ጋዜጠኛ ወይም ፊልም ሰሪ መረጃው ከአቅሙ በላይ እንደሆነበት አንዱ ማሳያ ነው። ጉዳዮችን ከሌሎች ጋር ይነጋገሩ፤ የታሰበበት ራስን የመንከባከብ ስልት ይከተሉ እና ሌሎችን በመርዳት ረገድ ምን ማድረግ እንደሚችሉ እና እንደማይችሉ ግልጽ ይሁኑ።**

ጥቁር አሜሪካዊው የዜጎች መብት ተሟጋች ኦድሬ ሎርድ በአንድ ወቅት እንዲህ ሲል ጽፏል፣

> እራስን መንከባከብ ራስ መውደድ አይደለም። ራስን ማዳን ነው…

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) መሸፈን ማለት የሰው ልጆች በሌሎች ላይ ሊያደርጓቸው የሚችሏቸውን አንዳንድ በጣም አስከፊ ነገሮችን መጋፈጥን ያካትታል። ጋዜጠኞች ራስን የመንከባከብ እና የስሜት-ቀውስ ግንዛቤን ለመወያየት ብዙ ጊዜ አያጠፉም፤ ምንም እንኳን ለህክምና ባለሙያዎች እና ሌሎች ከአደጋ ጋር ለሚሰሩ ሰዎች ቁልፍ አርእስት ቢሆንም።

መርሳት የሌለብዎት ነገር- እነዚህን ታሪኮች ለመዘገብ የሚፈልጉ ጋዜጠኞች እና የፊልም ባለሙያዎች ተነሳሽነት ያላቸው እና በጣም ጠንካራ ግለሰቦች መሆናቸውን ነው። ነገር ግን ይህ የሥራ መሰክ ለድካም፣ ለድባቴ (ዲፕሬሽን)፣ አደንዛዥ እፆች አላግባብለመጠቀም እና ከአስቃቂ ሁኔታ በኋላ ለሚከሰት ጭንቀት ከፍ ያለ ስጋቶችን አሉት።[ሀ]ተጽዕኖዎቹ ብዙም ከባድ ባይሆኑም እንኳ፣ የሥራውን አስቃቂ ይዘት በማወሃድ ላይ ያለው ችግር ቀድሞውኑ ተጋላጭ በሆኑ ምንጮች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

## ርህራሄ እንደ ባለ ሁለት መንገድ ድልድይ

ከሌሎች ጋር በርህራሄ የመገናኘት ችሎታ እና ያሉበት የስሜታዊነት ደረጃ መለካት ውጤታማ ጠያቂ የመሆን አስፈላጊ ችሎታ ነው። ሰዎች ልምዳቸውን ለመካፈል በቂ ግንዛቤ እና ደህንነት የሚሰማባቸውን ሁኔታ የምንፈጥረው ርህራሄ በምናሳይበት ወቅት ነው። እንዲሁም በአንድ ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን የምንረዳው እንዴት ነው – ነገሮችን በሌላ ሰው ጫማ [ሁኔታ] ውስጥ መቆም በመሞከር።

ርህራሄ በጠያቂውና ተጠያቂው መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ይከፍታል፤ ይህም ነገሮች ድልድዩን ተሻግረው ወደ ኋላ እና ወደ ፊት የሚሉበት መንገድ ይፈጥራል። ቃለ-መጠይቅ አድራጊ እንደመሆንዎ፣ እየሆነ ያለውን ነገር ሙሉ በሙሉ ሳያውቁ አንዳንድ ጊዜ ራስዎን

ሀ. የጥናት ዝርዝር እዚህ ማግኘት ይቻላል: https://dartcenter.org/content/covering-trauma-impact-on-journalists.

© Dart Centre Europe

የሌሎችን ስሜት ወስደው ሊያገኙት ይችላሉ። እንደ እፍረት፣ አቅመ ቢስነት እና ፍርሃት ያሉ ጠንካራ ስሜቶች ሰውር እና ለመከታተል በሚከብዱ መንገዶች ተላላፊ ሊሆኑ ይችላሉ። ጋዜጠኞች ከአስጨናቂ ቃለ መጠይቅ በኋላ በራሳቸው ላይ በድንገት ማዘን ያልተለመደ ነገር አይደለም።

በተመሳሳይ፣ ሰዎች እንዴት እንደሚጠቁ ወይም እንደሚሰቃዩ ተደጋጋሚ ምስክርነቶችን በመስማት ወይም በማንበብ ያልተጠበቀ ጊዜ ውስጥ ጣልቃ የሚገቡ አስተሳሰቦች እና ምስሎች ወደ ጭንቅላት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። እነዚህ ተፅዕኖዎች አብዛኛውን ጊዜ ለአጭር ጊዜ እና በአንጻራዊነት ቀላል እና በተወሰነ ደረጃም ከሰራው ጋር ተያይዞ የሚመጡ ናቸው – ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ እና ሥር ከገቡ የአእምሮ ጤና መዘዝ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ይህ ክስተት 'ቪካሪዮስ (vicarious) ወይም 'ሁለተኛ ሰቃይ' ተብሎ የሚጠራ ሆኖ ግጭትን በቀጥታ ከማየት ወይም ሰለባ ከመሆን ጋር ከሚመጡ ተጽእኖዎች ጎን ለጎን የሚከሰት ነው።

## ወደ ሌሎች ሰዎች ጭንቀት መሳብ

ጋዜጠኞች በፍፁም ስሜታዊነት እንዲኖራቸው አይገባም የሚል ንድፈ ሃሳብ አለ። ይህ ቀልብ የሚስብ ሀሳብ ቢሆንም፣ ነገሮች ግን እንደዛ አይሠሩም። በተወሰነ ደረጃ ላይ ጠንካራ የመጨነቅ ስሜት እና የመርዳት ፍላጎት ሊሰማዎት ይችላል። ያ ከሆነ፣ እንደ ጋዜጠኛ ገደብዎ ማወቅና እና ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ምን ማድረግ እንደሚችሉ እና እንደማይችሉ መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው። ድንበሮች በሚጎዱ መንገዶች ሊደበዝዙ ይችላሉ፡-

- ከሞያነት ይልቅ፣ የበለጠ ወዳጅነት ወዳለው አቅጣጫ መሳብ ሊሰማዎት ይችላል። የመርዳት ፍላጎት መኖር ችግር አይሆንም ነበር፤ ነገር ግን ሚናውን ለመወጣት የማይችሉ ከሆነ ከእውነታው የራቀ ነው። አደጋው፣ በማትወጣው እና የማያቋርጥ ስሜታዊ እና ቁሳዊ ድጋፍን ለማድረግ የውሸት ተስፋዎችን መገንባት ላይ ነው። ያስታውሱ፣ ባለማወቅ የሰዎችን ተስፋ መገንባት ቀላል ነው። የስሜት ቀውስ ባለበት ሁኔታ፣ እንደ መተሳሰር እና ክህደት ያሉ ጠንካራ ስሜቶች ሳይታዩ በውስጥ ነው የሚቆዩት። እንደ ጓደኛ ሳይሆኑ ሰብአዊነት ያለው ሰው መሆን እና በሥነ ምግባር መምራት ፍፁም ይቻላል።
- የወሲብ ጥቃት በራስዎ ላይም የተፈጸመ ሊሆን ይችላል። ይህ ጠቃሚ ግንዛቤን ሊሰጥዎት ይችላል ነገር ግን የደረሰዎት ጥቃት ምንጭዎ ከደረሳቸው ጋር የሚጣበቅበት ቦታ ላይ ሊጥልዎት ይችላል። ይህም ግን ሌላውን እንደ የተለየና ልዩ ሰው እንደሆነ የመረዳት ማስተዋልን እንዲያጡ ያደርጋቸዋል።
- ቃለ መጠይቁ ለምንጭዎ በሆነ መንገድ የሚፈውስ (ቴራፒዩቲክ)፣ ስነልቦናዊ እርዳታ የሚሰጥ (ካታርቲክ)፣ ወይም ኃይልን የሚሰጥ ሂደት ሊሆን እንደሚችል ለማመን በመፈለግ ወጥመድ ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ። እውነት ነው ተጎጂዎች በመናገር መፅናናትን ያገኛሉ፣ ሰዎችን ግራ ከሚያጋባ እና የሚያሰቃይ አጋጣሚ የሚወጡበት አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እንደ ሚዲያ ባለሙያ ይህንን ሊያረጋግጡ የሚችሉበት ምንም መንገድ የለም። በእርዳታ ማህበረሰቡ ውስጥ፣ ይህ 'የአዳኝ ውስብስብ' ተብሎ ይጠራል፣ እና ከባድ ችግር ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

የራስዎን ስሜት የመቆጣጠር ችግር ቃለ-መጠይቆችን ከሃዲዱ አስወጥቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊወስድ ይችላል። ለምሳሌ፣ ሰዎች እራሳቸውን ለመርዳት ብዙ ባለማድረጋቸው ልንበሳጭ እንችላለን፣ ወይም የሌሎችን ሰቃይ ደረጃ መሰጠት ልንጀምር እንችላለን፣ ይህ ደግሞ በጣም የከፋውን ብቻ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ እንዲታይ የሚያደርግ ነው።

## ለዚህ ሁሉ ምን ማድረግ ነው የሚሻለው?

መፍትሔው ርህራሄን ወይም ተልእኮውን መተው አይደለም። ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ የግል ስሜቶችን ማፈን አይጠቅምም። በተጨማሪ፣ ሁለቱም እራሳቸው የመቋቋም አቅም አካላት ናቸው። ይልቁንም ርህራሄን ከስልታዊ ዕረፍት የሚጠቀም ጡንቻ እንደሆነ አድርገው ያስቡ። ከሰራው ገለል ብሎ መቆየት እይታን ያሰፋል፣ እንዲሁም ራስዎን ጉልበት እንዲያገኙና ከሚያሰቅቅ መረጃ ራቅ እንዲሉ የሚያስችል ዕድል ይሰጣል። ከአዎንታዊ የሕይወት ገጽታዎች ጋር እንደገና መገናኘት አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ የሚከተሉት አንዳንድ ነገሮች ሊያግዙ ይችላሉ፡-

- **እራስዎን ከአስከፊ ነገሮች** (**እና በአጠቃላይ ስራን የሚያስታውሰዎትን ማንኛውንም ነገር**) **እንዲያርቁ የሚያስችሉዎትን እንቅስቃሴዎችን በየቀኑ ይገንቡ።** መሳጭ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ፣ መጽሃፍ ማንበብ ወይም ጭንቅላትን ከርዕሱ የሚያወጣ ማንኛውም ነገር፣ ሁሉም ጥሩ ምርጫዎች ናቸው። ንቃተ-እእምሮ ለብዙዎች የሚሰራ ሌላው አማራጭ ነው።
- **መደበኛ እረፍቶችን እና የእረፍት ክፍለ-ጊዜዎችን ያቅዱ።** በማንደክምበት ጊዜ የሚያስጨንቁን ነገሮች በተሻለ መንገድ መቋቋም እንችላለን።
- **የሰውነትን ሚዛን ይጠብቁ።** የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ ዘርጋ ማለት፣ የአተነፋፈስ ልምምዶች፣ በቂ እንቅልፍ እና ተገቢ አመጋገብ ሁሉም እየተወጠረ እና እየጨመረ ያለዉ የጭንቀት መከማቸትን የማስወገድ ውጤታማ መንገዶች ናቸው።
- **ስለሚያስጨንቁ ጉዳዮች ከባልደረባ፣ አማካሪ ወይም ጓደኛ ጋር ይነጋገሩ።** አንዳንድ ጊዜ ድምፅ የሚያጎላ ከሌለ ነገሮችን በግልፅ ማየት ከባድ ነው። ተመሳሳይ እርዳታ የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ወደ እርስዎ የሚመጡ የሥራ ባልደረባ ከሆኑ፣ ችግሩን ለመመርመር ዕድል ከማግኘታቸው በፊት ችግራቸውን ለመፍታት ከመቸኮል ይልቅ ጥሩ አድማጭ ይሁኑ። ማስታወሻ እና ሌላ

ግላዊ ጽሑፍ መጻፍም ሊረዱ ይችላሉ።

- **ከተፈጥሮ ጋር ግንኙነት ያድርጉ።** በተለይ ይህ ብዙ ሰዎች ጠቃሚ ሆኖ አግኝተውታል።
- **ከስህተት-መማር የሚለውን አዎንታዊ አመለካከት ይከተሉ።** ነገሮች ከተሳሳቱ፣ ከአደጋዎች እና ደካማ ውሳኔዎች ከመድገም ይልቅ ለመማር ይወስኑ።

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አብዛኛው የመከላከያ ልማዶችን ስለመፍጠር እና ውጥረቶች በሚጨምሩበት ጊዜ እነሱን አለመተው ነው። በመስክ ላይ ሆነው እና መደበኛ ባልሆኑ ሰዓታት በሚሰሩበት ጊዜ እንኳን፣ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎ ውስጥ አንዳንዶቹን መለማመድ ይችላሉ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ማህበራዊ ድጋፍ ለመቋቋም ትልቁ አስተዋፅዖ ምክንያት ሊሆን ይችላል።[ለ] ከመጠን በላይ ገለልተኛ ከመሆን እና ማንኛውም አይነት ከልክ ያለፈ ራስን የመፈወስ እርምጃዎች፣ በመድኃኒት ይሁን ወይም ከመጠን በላይ በመስራት ይጠንቀቁ። **ሚዛን መጠበቅ ቁልፍ ነው።**

## ሽግግሮችን ማስተዳደር

የአገር ውስጥ ጋዜጠኛም ሆኑ ወይም ወደ አንድ አገር የሚገባ እና የሚወጣ የውጭ አገር ዜጋ፣ በሕይወትዎ ባለው አንጻራዊ የተሻለ መብትና እና ሌሎች ባሉበት ሁኔታ መካከል ያለው ልዩነት በተለይ ሽግግርን አስቸጋሪ እንደሚያደርግ ሊሰማዎት ይችላል።

በዚህ ርዕስ ላይ ከሚሰሩ የሚዲያ ባለሙያዎች መካከል የአቅም ማነስ (ስቃይ ለማስቆም የሆነ ነገር ማድረግ ባለመቻል) እና የጥፋተኝነት (ወደ ቤት መመለስ በመቻላቸው) ስሜት መኖር የተለመዱ ናቸው። ለእነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ምንም ቀላል መልሶች የሉም፤ ነገር ግን እነሱን መጋፈጥ ተጠቃሚ መሆን ይችላል። ምናልባት እራስዎን እንዲህ ብለው ይጠይቁ፡- "ስለማልቆጣጠራቸው ነገሮች በራሴ ላይ ጫና መፍጠር ምንጮቼን መርዳት ወይም የበለጠ አስፈላጊነት ያለው ስራ መፍጠር ነውን?"

ለራስዎ ርህራሄ ሳይኖርዎት ለሌሎች ሩህሩህ መሆን ከባድ ነው። ርዕሱ በጨለመ ቁጥር፣ ወደ ኋላ መግፋት እና እርስዎን ብርታት የሚሰጡ ትናንሽ አወንታዊ ነገሮችን ለማግኘት መስራት የበለጠ አስፈላጊ ነው። እንደገናም፣ እነዚህን ጉዳዮች ከሚረዱ ሰዎች ጋር መነጋገር ሊረዳ ይችላል።

## ተጨማሪ መረጃዎች፡ ራስን መንከባከብ

የዳርት ማእከል **ከአስቃቂ ምስሎች** ያካተተ ስራ በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ አለው። **ጠለቅ ባሉ ምርመራዎች ወቅት አስቃቂ ምስክርነቶችን** ስለመቆጣጠር እና በህፃናት ወሲባዊ ጥቃት ታሪኮች ላይ በሰሩ ጋዜጠኞች እና የፊልም ሰሪዎች መካከል ስለራስ እንክብካቤ የተደረገ **ውይይት** ይህንን የታመቀ ጠቃሚ ምክር ይመልከቱ። በክፍል **ቀ.1** እንደተጠቀሰው ሥራ አስኪያጆች **ይህንን መመሪያ** ሊመለከቱ ይችላሉ። **ይህ የድረ-ገጹ ክፍል** የአቻ ድጋፍን ሚና ጨምሮ ድርጅታዊ ጉዳዮችን በበለጠ ዝርዝር ይመለከታል።

እንነጋገር፡- የግል ድንበሮች፣ ደህንነት እና ሴቶች በጋዜጠኝነት (Personal Boundaries፣ Safety and Women in Journalism ) ለሴት ጋዜጠኞች ጾታዊ ትንኮሳን ስለመቆጣጠር ምክር ይሰጣሉ። ለድንበር-የለሽ ጋዜጠኞች (ሪፖርተርስ ሳንስ ፍሮንትይየርስ) ተብሎ በዳርት ሴንተር የተዘጋጀው ይህ **ጠቃሚ ምክር** በግጭት ቀጠና ውስጥ ለሚሰሩ ጋዜጠኞች የተለየ የራስ እንክብካቤ ምክር ይሰጣል። በመጨረሻም፣ የወሲባዊ ጥቃት ታሪኮች ብዙ ጊዜ በኢንተርነት መረብ ላይ ለሚገኙ በጥባጮች (ትሮልስ) እና ለሌሎች ክፉ ተዋናዮች የሚሰብ ማግኔት በመሆናቸው፣ **በዲጂታል ራስን-መከላከል** ላይ አንዳንድ ሀሳቦች እዚህ አሉ።

ይህንን ጽሑፍ ያጋሩ

**ለ.** ይመልከቱ፡ S. M. Southwick and D. S. Charney፣ Resilience: The Science of Mastering Life's Greatest Challenges (Cambridge: Cambridge University Press፣ 2012)፣ especially chapters 4፣ 6 and 7.(Cambridge: Cambridge University Press, 2012), especially chapters 4, 6 and 7.

እባክዎን በግራፊክ መደብ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ ብቻ ያትሙ

# #7.

ዘገባውን ማቅረብ

# ያስታውሱ፤ ጾታዊ ጥቃት መቼም ቢሆን የታሪኩ ብቸኛ ገጽታ አይደለም።

# #7.

ዘገባውን ማቅረብ

## ያስታውሱ፤ ጾታዊ ጥቃት መቼም ቢሆን የታሪኩ ብቸኛ ገጽታ አይደለም።

በክስተቶች ጭካኔ ላይ ብቻ ማተኮር ምንጮቹን እና ጋዜጠኝነትን ሊጎዳ ይችላል። ለክስተቱን ጠቅላላው ሁኔታ ትኩረት ይስጡ።

በጦርነት ውስጥ የጅምላ አስገድዶ መድፈር ወይም ጾታዊ ብዝበዛን የመሳሰሉ አሰፈሪ ድርጊቶች ሲያጋጥም ትኩረቱን በጾታዊ ጥቃት እና በሚያስከትለው ጉዳት ላይ ማተኮር የማይቀር ሆኖ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን የክስተቱ ስፋነት ማምጣት አለመቻል ዘገባዎን የሚያሳንስ፣ ተመልካቾችን የሚያሳጣ እና የተረፉትን የሚያገል ነው። ታሪኩን በሚከተሉት መንገዶች ማስፋትዎን ያረጋግጡ፦

- የጉዳተኞችን ሕይወት በተመለከተ የተሟላ ዘገባ ይስጡ። መወደቅን ላለመተንበይ ወይም ሰዎችን ወደደረሰባቸው አስከፊ ነገሮች አሳንሰው እንዳያዩ ይጠንቀቁ። የማገገም ሂደታቸው ሊያወሳሰበው ይችላል።
- ከአስገድዶ መድፈር ያለፉ ሌሎች ወንጀሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስቡ። ጉዳተኞች የሚወዷቸው ሰዎች እና ቤታቸውን ሊያጡ እና በግዳጅ ሊፈናቀሉ ይችላሉ። እነዚህ ነገሮች ለሰዎችም አስፈላጊ ናቸው።
- ለተጎጂዎች የሚሰጥ ህዝባዊ ርህራሄ ሊገድቡ ስለሚችሉ፣ ታሪኩን ወሲባዊ ስሜት ሊፈጥር ወይም ስሜት ቀስቃሽ እንዲሆን የሚያደርጉ ዝርዝሮች ላይ ከመጠን ያለፈ ትኩረትን ማድረግ ያስወግዱ።
- ሙሉ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ሁኔታን በማቅረብ ተከታታዮችን የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እንዲያዩ እርዷቸው።

ብዙ ጊዜ ምን ያህል ስራችን በጉዳተኞችን ህይወት ተመልሶ በሚድኑበት ሂደት ላይ ተጽእኖ እንደሚኖረው እንዘነጋለን።

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ከከፍተኛ የሰነ ልቦና እና የአካል ጉዳት ጋር የተያያዘ ነው። የጾታዊ ጉዳት መዘዝ ብዙውን ጊዜ ጠንካራ የመለያየት ስሜቶችን ያመጣል። ሰዎች ከራሳቸው እና ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ከነበሩት ሰው እንዲሁም ከሌሎች ጋር እንደተለያዩ ይሰማቸዋል። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ከሰፊው ማህበረሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲቋረጥ የማድረግ አቅም ስላለው፣ ጉዳተኞች እንዲገለሉ እና የድጋፍ እድሎችን እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል።

በሌላ በኩል ማገገም የዚህን ተቃራኒ ይመስላል። ይህ መልሶ ግንኙነት በመፍጠር ሊሆን ይችላል- ሰዎች ሌሎች እነርሱን መንከባከብ እና በክብር መያዝ እንደሚችሉ ሲያምኑ።

እንደ ሚዲያ ሠራተኞች፣ ግለሰቦችን ማዳን የእኛ ድርሻ አይደለም። የእኛ ሥራ ጉዳተኞችን በግል መንገድ እንደሚያበረታታ መገመት ጥበብ የጎደለው እና እነሱን ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ ነው- ይልቁንም ሳናስበው በእነዚያ የመለያየት ኃይሎች ላይ እንዳንጨምር መጠንቀቅ አለብን። በምስራቅ አፍሪካ የምትሰራ አሜሪካዊቷ ጋዜጠኛ ጂና ሙር እንዲህ ትላለች፦

> በምናወጣው ዘገባ ውስጥ – ከቀናት ፣ ወራት ፣ ዓመታት ብቅ ብሎ፣ እነሱን የሚያሸማቅቅ ወይም የሚያሰጋ ምንም ነገር እንደሌለ ማረጋገጥ አለብን. . .ዓለም ስለእነርሱ የሚያውቀውን እንዲገነዘቡ ለማድረግ የአሰቃቂዉን ታሪክ ዝርዝር ለተጎዱትን ደግመን እናብራራለን።[ሀ]

ለተመልካቾች የምንልካቸው መልዕክቶች እዚህ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በየቦታው ስለ ወሲባዊ ጉዳት ውይይቶች በአፈ ታሪኮች፣ መገለሎች እና የማይጠቅሙ አስተሳሰቦች የተሞላ ነው። እነዚህን ማጠናከር ሆነ ማጋለጥ እንችላለን – ጋዜጠኞች እና ፊልም ሰሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ገለልተኛ ተመልካቾች አይደሉም። ለዚህም ነው የግጭቱ አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ገጽታዎች ላይ የተሟላ ዘገባ ማቅረብ አስፈላጊ የሆነው።

ሀ. በጂና ሙር ጽሑፍ: The Pornography Trap

© Dart Centre Europe

## በአንድ የታሪኩ ጥግ ላይ የመጥፋት አደጋ

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) በተለያየ መልኩ ይመጣል፣ ነገር ግን በጣም የሚሰበው ባህሪው ብዙውን ጊዜ የጭካኔው ነው። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንደ ፊልም ሰሪ ወይም ጋዜጠኛ፣ እርስዎ በሰሙት መጥፎ ነገር ተመልካቾችን ለማስደንገጥ፣ ይህ እንደሚያነቃቃቸው በማሰብ፣ ጠንካራ እና የማይገርም ፍላጎት ሊለማመዱ ይችላሉ።

ነገር ግን እዚህ ያለው አደጋ ይህ በተቃራኒውን ሊያሳካ ይችላል። በወሲባዊ ጥቃት አሰፈሪነት እና ዝርዝር ላይ ብዙ ትኩረት መስጠት ተመልካቾችን ከግጭት ጋር በተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ለተጎዱ ሰዎች ያለውን ርህራሄ ሊቀንስ በሚችል መንገድ ከመከታተል ዘወር እንዲሉ ያስገድዳቸዋል። በቂ ተጨባጭ መረጃ ካላቀረቡ ተመልካቾች የእነዚህን ወንጀሎች ባህሪ እና የሚያስከትለው ነገር አይረዱም።

በግብፅ ውስጥ ጾታዊ ጥቃትን እና የመንግሥትን በፅናት ላይ ያለውን ሚና የሚዳስስ ለቫሰ [መጽሔት] ፖድካስት መስራች ስቴፋኒ ካሪዩኪ እነዚህ ውሳኔዎች ጥንቃቄ የተሞላበት ሚዛን ያስፈልጋቸዋል ይላል፦

> ምን ያህል ጠለቅ ብለን መግባት እንደምንፈልግ ለመወሰን ወዲህ እና ወዲያ ብለናል? ለምን ዝርዝሮችን እንሰጣለን፣ በእርግጥ አስፈላጊ ናቸው? በአንዲት ሴት ጉዳይ ላይ፣ የሕክምና መርማሪዎቹ በተለያዩ የመጀመሪያውን በደል በሚያንፀባርቁ አኳኋን እንድትሆን በማድረግ እርቃኗን እያሉ ብልቷን ደጋግሞ መረመሩ። የተጠቀምንበት የመጨረሻው ኦዲዮ ይህንን በግልጽ የሚሳይ ነው። ነገር ግን እኛ እንደዚህ ያህል በዝርዝር የገለፅንበት ምክንያት ይህ እሷ የምታደርገው ምርመራ እስከ አሁን ድረስ መንግሥት በሴቶች ላይ ለአሥርተ ዓመታት ሲያደርግ የነበረውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው።[ለ]

በእርግጥም፣ ስለአስቃቂ ሁኔታ ውጤታማ ጽሁፍ ለማቅረብ እርስ በርስ የሚጋጩትን የተለያዩ ጉዳዮችን እንዴት ማመጣጠን እንደሚቻል ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል። ለምሳሌ፦

- **ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ምን ያህል በሰዎች ህይወት ላይ ጉዳት፣ አቅመ ቢስነት እና መቆጣጠር ማጣትን የሚያመጣው? ምን ያህል ስለ መቃወም እና ማገገም ነው- ለመትረፍ ምን ጠየቀ?**

ምንም እንኳን ሁኔታው አስከፊ እና ተስፋ-ቢስ ቢመስልም፣ ጉዳተኞች በህይወታቸው ውስጥ አዎንታዊ ነገሮች አሏቸው። አስፈሪ እና ፍጹም አቅም ማጣት ብቻ በሰዎች ላይ ማንጸባረቅ ትክክልም ጠቃሚም አይደለም።

- **ምንያ ያህል ለአንድ ሰው ስለደረሰበት ግላዊ ክስተት ነው፣ ምንስ ያህል እና ስለ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ፡ በተለይም ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች?**

አጠቃላይ ሁኔታ ላይ በቂ ትኩረት ካልሰጡ፣ ታሪኩ ሰብአዊ ገጽታ ያለዉ አሰገራሚ እና አሰጨናቂ ሊሆን ይችላል – የትኛውም ትክክለኛ ዓላማ የሌለው እና ለተመልካቾች ምን እየተከሰተ እንዳለ ወይም መፍትሄዎች የት እንደሚገኙ ግንዛቤን የማይሰጥ ዓይነት። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ምንም በሌለበት ውስጥ አይከሰትም – እንደ ርዕሰ 'በጦርነት ውስጥ መደፈር' ግጭቱን የሚያንቀሳቅሱትን ኃይሎች ሳይጠቅስ ሊታወቅ አይችልም።

ነገር ግን ለግለሰቦች እና ለግል ሁኔታቸው በጣም ያነሰ ትኩረት መስጠት ክብር የጎደለው ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም አንድ ሰው ለየት ያለ ቁጥር ለማሳየት ብቻ የተካተተ ነው የሚል ስሜት ሊፈጥር ይችላል።

## ተቀናቃኝ ውጥረቶችን መደራደር

እያንዳንዱ ጉዳይ የተለያዩ ተከታታይ የማመጣጠን እርምጃዎችን ይፈልጋል። ይህንን መገንዘብ ብዙ ጊዜ የተወሳሰበ ነው ምክንያቱም ብጥብጥ መጥፎ ተጽዕኖ ሊያሳድር እና ቀሪው የማይጠቅም ወደሚመስለው አቅጣጫ ይጎትተናል። አሰጊ እና አሰቃቂ ይዘት የሁለትዮሽ አስተሳሰብን ያሰፋፋል፣ በዝርዝሮች ወይም በተገደቡ ማዕዘኖች ላይ መጣበቅ በጣም ቀላል ነው።

በሚጽፉበት ጊዜ ወይም በሚያድቱበት ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባት ያለብዎት አጭር የማረጋገጫ ዝርዝር እነሆ፦

- ይህ ከሚገባ በላይ ወደ አካላዊ ወይም ግላዊ (ወሲባዊ) ሰዕላዊ መግለጫ የሄደ ነውን?
- መግለጫውን ወሲባዊ የማድረግ አደጋ (እንዲያውም ባለማወቅ ለጥቃት መነሳሳትን ስበብ) ሊሆኑ የሚያስችሉ የአንድን ሰው አካል፣ ገጽታ፣ ልብስ ወዘተ አሉ?
- የእኔ ትረካ ወደፊት የአንድ ግለሰብ ወይም የማህበረሰብ ውድመት ይተነብያል? ምንም እንኳን ነገሮች ተስፋ-ቢስ ቢመስሉም፣ ማገገም የማይቻል መሆኑን መግለጽ ትክክል ያልሆነ እና አሰቀድሞ መፍረድ ነው። (ከጨለማው ውጭ የሆነ ነገር ለማየት ከተቸገሩ እራስዎን ይህ ሰው ከደረሰበት ውጭ ማን እንደሆነ ይጠይቁ። ብርታት እና ድጋፍ ከየት ያገኛሉ?)
- ወይም፣ በጣም ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ እየዞርኩ ነው፣ እንዲሁም ተሰፋ አሰቆራጭ ሁኔታን በሰው ሰራሽ መንገድ ለማቃለል

ለ. ካሪዩኪ በዚህ ጥናት ተሳትፈዋል

የውሸት ብሩህ ተስፋን እየሰጠሁ ነው? ከትክክለኛነቱ ውጭ፡ ብርታታትን የሚያጋንን ጋዜጠኝነት ሰዎች ያሉበትን የተገለጸውን ሁኔታ የማይገነዘቡትን ሰዎች ሊነጥል ይችላል።

- የሰራሁት ዘገባ የሁለቱም የወንጀለኞች እና የተጎዱትን ድምጽ የሚያጠቃልል ከሆነ በእኔ ትረካ ውስጥ የወንጀለኞችን አመለካከት ማእከል የሚያደርግ ወይም ስልጣናቸውን የሚያሰፋ ነገር አለ? (ይህን በትክክል ማወቅ ውስብስብ ነው። እነዚህን ድምፆች ወደ ተለያዩ ዘገባዎች መለየት የበለጠ ቀላል ሊሆን ይችላል።)
- የሰራሁት ዘገባ ሰዎች በግጭት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ሌሎች አስቃቂ ጉዳቶች በማግለል መደፈር ላይ ያተኩራል? ሰዎች ዘመዶቻቸው ሲገደሉ እና ቤታቸውንና መተዳደሪያቸውን ሲያጡ አይተው ይሆናል። አዲስ ሕይወት ለመገንባት የሚታገሉ ስደተኞች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ለሰዎች አስፈላጊ ናቸው፣ ጋዜጠኞች የኪሳራዎቻቸውን አንድ ገጽታ ብቻ ማተኮራቸው ተጎጂዎች ላይረዱ ይችላሉ።

## ታሪኩን ማቀናበር፡ ለአዘጋጆች የሚመለከቱ ማስታወሻዎች

አንድ ታሪክ የተቀነባበረበት መንገድ – ርዕሱ ፣ የፎቶ መግለጫዎች ፣ ፊልም ለማስተዋወቅ የሚያገለግሉ ምስሎች፣ ማጠቃለያ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የቀረቡበት መንገድ – ታሪኩ እንዴት እንደሚታይ እና በእሱ ውስጥ በተካተቱት ሰዎች ውጤቱ ምን እንደሆነ ላይ ትልቅ ተፅእኖ ሊኖረው ይችላል።

አንድ ግልጽ አደጋ ታሪኩን ወሲባዊ ማድረግ ነው – እውነተኛውን አጠቃላይ ሁኔታን እውነተኛ እንዳልሆነ በሚመስል መልኩ ስሜት ቀስቃሽ ያደርገዋል። በወሲባዊ ጥቃት ውስጥ፣ ወሲብ ሊከሰት ይችላል – ነገር ግን እነዚህ ታሪኮች በምንም መልኩ ስለ መደበኛ ወሲባዊ እንቅስቃሴ አይደሉም።

እንደ 'የወሲብ ባሮች' ያሉ ቃላት ወሲብ ቀስቃሽ ስለሆኑ ጥቃትን ወደ መዝናኛነት የመቀየር አደጋ አላቸው። እንደ 'የልጆች ሙሽሮች' ያሉ አገላለጾች በተሻለ ሁኔታ እንደ 'አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ጠለፋ እና ጾታዊ ጥቃት'፣ በሴተኛ አዳሪነት የተገደደች ሰው 'የሴት ጓደኛ' አይደለችም።

በላቲን አሜሪካ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) በሰፊው የፃፈችው ጂኒት ቤዶያ፣ በነፍጠኞች የሚፈፀሙ የፆታዊ ጥቃት ዘዴዎች ተገቢ ካልሆነ እና ጊዜ ያለፈባቸው ቋንቋዎች እንዴት እንደሚሸፈኑ እዚህ ገልፃለች፡-

> ጋዜጠኞች ስለ አሰገድዶ መድፈርን ወይም ሴትን መግደልን ሲናገሩ 'የስሜት ወንጀል' ብለው ማውራትን ለማቆም በሚዲያ ዘንድ ብዙ ዘመቻ አድርገናል።
>
> ህብረተሰቡ አሁንም አሰገድዶ መድፈር እንዲት ሴት ሆን ብላ በአጥቂዋ ላይ ከምታነሳው የፆታ ቅስቀሳ ጋር የተያያዘ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራል። ስለዚህ 'ስሜታዊ' ተብሎ ይገለጻል። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እዚህ ያለው ቅሰቀሳ፣ በዚህ ዓይነት ጋዜጠኝነት ውስጥ የተካተተው እንዲህ ዓይነት ወንጀሎች የሚፈጸሙት 'በፍቅር' ስም ነው የሚል ነው።
>
> በብዙ የፍርድ ቤት ችሎቶች ውስጥ የሚያፍሩ ወንዶች በዚህ ክርክር እራሳቸውን ሲከላከሉ ሰምቻለሁ። 'ስለወደዷቸው' የፆታ ጥቃት እንደፈጸሙባቸው ወይም እንደገደሏቸው ይናገራሉ።

እንዲሁም አሰገድዶ መድፈርን እንደ የማይቀር የጦርነት መዘዝ አድርጎ መቅረቡ ተረት መሆኑንም ልብ ይበሉ። የሚያሰቀጣ የጦር ወንጀል ከመሆን በተጨማሪ፣ በሁሉም ግጭቶች፣ መደበኛ ያልሆኑ ተዋጊዎች በሚሳተፉበት ጊዜም እንኳ እንደማይሰፋፋ ጥናቶች ያሳያሉ። [ሐ]

እነዚህን ጉዳዮች ለማንፀባረቅ የእራስዎ የውስጥ ዘይቤ መመሪያ ማዘመን እንደሚያስፈልገው ያስቡበት። በቻሉ ጊዜ ሁሉ ለድጋፍ ድርጅቶች ግብዓቶችን እና ለማንኛውም የፆታዊ ጥቃት ሰለባ የሆነች ግለሰብ ጽሑፋን ለማንበብ ወይም ለማየት ጠቃሚ ሊሆን የሚችል መረጃን ያካትቱ።

ሐ. Carlo Koos (2017) Sexual violence in armed conflicts: research progress and remaining gaps፣ Third World Quarterly፣ available here.

© Dart Centre Europe

## ተጨማሪ መረጃዎች

**በወሲባዊ ወጥመድ (In The Pornography Trap)** በሚል ጽሑፏ ውስጥ ጂና ሙር ቋንቋውን ማስተካከል ስላጋጠሙት ተግዳሮቶች ተወያይታለች። ይህ ከቺካጎ ግብረ ኃይል በልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን (Chicago Taskforce on Violence Against Girls & Young Women) የመረጃ **ሰብሰብ (Toolkit)** በአጠቃላይ ስለ ጾታዊ ጥቃት ዘገባ ያብራራል እና የቋንቋ ምርጫዎችን የሚያንፀባርቅ ክፍል አለው።

ይህ ከብሔራዊ የፆታዊ ጥቃት መረጃ ማእከል (National Sexual Violence Resource Center) የወጣ **የጥቆማ ወረቀት** ሁሉንም አይነት ጾታዊ ጥቃቶችን የሚሸፍን ሆነ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ብቻ ያተኮረ አይደለም። ቢሆንም፣ ስታቲስቲካዊ አውድ-መር አካሄድን የመውሰድን ኃይል ያሳያል።

በዳርት ማእከል ድረ ገጽ ላይ **ኒና በርማን** አጠቃላይ ሁኔታን ግምት የማስገባት አስፈላጊነት እና ተገቢ የእይታ ምርጫዎችን በማድረግ ላይ ትዳሰሳለች - ይህ ሁሉ በሚቀጥለው ክፍል በበለጠ ዝርዝር ተሸፍኗል።

ይህንን
ጽሑፍ ያጋሩ

© Dart Centre Europe

እባክዎን
በግራጫ መደብ ላይ
የሰፈረውን ጽሑፍ
ብቻ ያትሙ

# #8.

ዘገባውን ማቅረብ

# ምስሎቹ አይጠፉም፤ በእይታ ምርጫዎች ይጠንቀቁ

© Dart Centre Europe

ዘገባውን ማቅረብ

# #8. ምስሎቹ አይጠፉም፤ በእይታ ምርጫዎች ይጠንቀቁ

ምስሎች አንዴ ከወጡ በኋላ ሊመለሱ አይችሉም። ሁለንተናዊ የበይነመረብ መዳረሻ ሰዎችን ወደ ብዙ አይነት አደጋዎች ሊያስገባ ይችላል።

**ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ሲዘግቡ፣ የሚያደርጓቸው የእይታ ምርጫዎች - በተቀረጹ ቀረጻዎች ወይም በፎቶግራፎች ላይ - ሁሉም በጣም አስፈላጊ ናቸው። በተለይ አሁን፣ በዲጂታል ዘመን፣ ምስሎች እየሰሩበት ካለው ታሪክ ያለፈ ረጅም ህይወት አላቸው። ጉዳተኞችን በእይታ እንዴት እንደሚቀርቡ እና ምን እንድምታዎች እንዳሉዋቸው ሙሉ በሙሉ እንዲገነዘቡ በጣም አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት፦**

- **የተጎጂዎችን ማንነት ለመግለጽ የሚያስገድድ ጠንካራ ምክንያት አለ ወይስ በስም-አልባነት መጀመር የበለጠ ደህንነትን ይጠብቃል?**
- **ፎቶግራፍ ለመነሳት ወይም በቪድዮ ለመቅረጽ ትርጉም ያለው ስምምነት ሰጥተዋል? በማኅበረሰባቸው ውስጥ ሊታዩ የሚችሉትን የማኅበራዊ ሚዲያ ተደራሽነት ተረድተዋል?**
- **በምስሉ ላይ ባለማወቅ ማንነታቸውን ሊገልጽ የሚችል ነገር አለ?**
- **በመጨረሻው ቅንብሩ ምቾት እንዲኖራቸው በምስል ስራው ላይ እንዴት እነሱን ማሳተፍ እችላለሁ?**

> በግልጽ ልናገር – የግጭት አስገድዶ መድፈር ምስሎችና እና የአስገድዶ መድፈር ጉዳተኞችን በሰፋት መስራት እና መታየት አለባቸው። ምንጮችን የሚከላከሉበት፣ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታን በሚያከብሩ፣ የተጭበረበሩ አመለካከቶችን በማያስቀጥሉበት እና በሚዲያ ኩባንያዎች ለተጎጂዎች እንደ አንዳንድ አስማታዊ elixirs በማያቀርቡበት መንገዶች በተለየ መስራት አለባቸው።
> ኒና በርማን [ሀ]

ምስሎች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ላይ ጨምሮ የግጭት ዘገባ ዋና አካል ስለሆኑ ከአንባቢዎች ጋር ለመገናኘት አደገኛ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ተጎጂዎችን መልሶ ለመጉዳት ትልቅ ዕድል አለ፣ ይህም እነሱን ቃለ መጠይቅ ከማድረጋቸው የሚያያዝ አደጋ በላይ ነው።

የምስል እውቅ አባባሎች የተለመዱ ናቸው – ጉዳተኞችን እንደ ተገለሉ እና ግፍ እንደደረሰባቸው፣ ከራሳቸው አካባቢ የተወገዱ እንደሆኑ፣ ወይም በአካል ላይ ከፍተኛ ትኩረትን ማሳየት። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ ይህ ከቅኝ ግዛት እና ከባርነት የዘለቀው የዘረኝነት ምስል ታሪክ ውስጥም ሊገባ ይችላል። ምስልን የማንበብ ችሎታ መኖር ይህንን ለመረዳት ወሳኝ አካል ነው።

ከዚህም በላይ ምስሎች በዲጂታል ዘመን፣ በተለያዩ መሳሪያዎች ላይ እና በመድረኮች ላይ በቀላሉ ይጋራሉ፣ ይህም ማለት ጉዳተኞች በሩቅ ማህበረሰቦች ውስጥ ቢኖሩም ለረጅም አመታት በእነሱ ሊሰቃዩ ይችላሉ። እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ የባልካን ጦርነቶች ውስጥ ሴቶች መደፈራቸውን ለባሎቻቸው ሳይነግሩ ያገቡባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። ከአስርተ አመታት በኋላ የመዝገብ ቤት ሰነዶች በኢንተርነት ድህረ-ገጾች ላይ ሊገኝ ይችላል የሚል ሀሳብ የነበራቸው ጥቂቶች እንኳን አልነበሩም።

የዲጂታል ዘመን በምስል የሚመሩ ዘገባዎች የሚበዙበት ሁኔታ እየፈጠረ ስለሆነ፡ በአዘጋጆች እና ፎቶግራፍ አንሺዎች ላይ በጣም አስደንጋጭ እና ትኩረትን የሚስብ ምስል እንዲሰሩ የሚያሳድሩት ጫና ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ይህ የጉዳተኞችን አካል ወሲባዊ የማድረግ ወይም አስፈላጊ ባልሆነ መንገድ ማንነታቸውን ማጋለጥን ሊያስከትል ይችላል።

ቀደም ሲል በስምምነት ክፍል ቁ.3 ላይ እንደተብራራው፣ ምንጮችን እንዴት እንደሚገለጹ በሚወስኑ ውሳኔዎች ላይ ማሳተፍ ጥሩ ልምምድ ነው።

---

**ሀ.** ኒና በርማን በቦዝኒያ እና አፍጋኒስታን ግጭቶችን የዘገበች የዘጋቢ ስዕል አንሺ ነች። ለዚህ ፕሮጀክት በተደረገ ምርምር አስተዋፅዖ ያበረከተች ስትሆን፡ በግጭት እና በሰላማዊ ጊዜ የፎቶግራፍ ሥነ-ምግባር ላይ የጻፈች እና በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት ፕሮፌሰር ነች። ለተጨማሪ፡ እዚህ ይመልከቱ፡ https://dartcenter.org/resources/visual-choices-covering-sexual-violence-conflict-zones

© Dart Centre Europe

የያዚዲ ሴቶች በአይ ኤስ ሲደፈሩ የሚዘግቡ ጋዜጠኞች ፊታቸውን ተከናንበው ፎቶ በማንሳት ስማቸው እንዳይገለጽ ዋስትና እንደሚሰጡ ገምተው ነበር፤ ነገር ግን እንደ እውነቱ ከሆነ በማኅበረሰባቸው ውስጥ በቀላሉ በዓይናቸው እና ልዩ በሆኑ ፎጣቸው ተለይተው ይታወቃሉ።

## የበለጠ ውጤታማ እና ሥነ ምግባራዊ የእይታ ምርጫዎችን ማድረግ

የፎቶ ጋዜጠኞች ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው ምስል ለማግኘት ብዙ ጊዜ ከቢሯቸው ከሚመጣ ጫና ውስጥ እየሰሩ ቢሆንም፣ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) የደረሰባቸው ሰዎችን በማይጎዳ መልኩ እና የተለመዱ አባባሎችን በሚሰያወግድ መንገድ፣ ጊዜው ጠባብ በሆነበት ጊዜም እንኳን ቢሆን ምስሎች መስራት ይቻላል፤

እያነሷቸው ስላሉት ምስሎች ራስዎን መጠየቅ ያለብዎት አንዳንድ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የተጎጂዎች ማንኛቸውም ምስሎች ስም-አልባ ይሆናሉ እና የሚገለጹት ይህን ለማድረግ የሚያስችል ጠንካራ ምክንያት ካለ ብቻ ነው በሚል ግምት መጀመር ትችላላችሁ? መድረሻዋ ላይ ከመድረስዎ በፊት ይህንን ከአዘጋጁ ጋር በዝርዝር ለመወያየት ያስቡበት።
- የተጎጂዎችን ማንነት የማያሳዩ ምስሎችን ለመስራት ብዙ ኃይለኛ እና የፈጠራ መንገዶች አሉ። እነዚህን በደንብ አስቀድመው ማሰብ የተሻለ ነው። ምናልባት ሌሎች የተጠቀሙበት የተሳኩ በርካታ መንገዶች በተመለከተ የዲጂታል ማስታወሻ ደብተር ይያዙ።
- ታሪኩ ስለ አሰገድዶ መድፈር ከሆነ፣ ተጎጂዋን አካል እንዴት እየገለጹት እንደሆነ ግንዛቤ ይኑሩዎት። ትኩረትን ወደ የትኛው የሰውነት ክፍል እየሳቡ ነው? ስለ ሰውዬው እንደ ወሲባዊ ቁስ የሚወሰድ ማንኛውንም አመለካከት እንዴት ማስወገድ ይችላሉ?
- ሰውዬው ብቸኛ ወይም የፈረሰ እንደሆነ የሚጠቁሙ ምስላዊ የተለመዱ አባባሎችን ለማስወገድ ይሞክሩ። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ከመጠን በላይ መነጠል የታሪኩ እውነታ ሊሆን ይችላል፣ ግን አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች ሰፋ ያለ የድጋፍ ሁኔታ አላቸው – እናም ያንን ማንጸባረቅ የበለጠ ትክክል ነው።

ማንነትን ለመደበቅ አሃዛዊ ቴክኒኮችን እየተጠቀሙ ከሆነ ማደብዘዝ ብቻ ሳይሆን ኦሪጅናል ፒክሰሎች ከምስሉ ላይ መወገድ አለባቸው። እንዲሁም፣ ቦታን የሚለይ ፋይል ውስጥ ምንም ሜታዳታ አለመኖሩን ማረጋገጥ አለቦት። ምስሎች በሚነሱበት ጊዜ እነማን ሊኖሩ እንደሚችሉ እና ለምን እንደሆነ ማሰብም አስፈላጊ ነው። ሊታሰብባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነጥቦች እነሆ፡-

- ምንጮቹ፡ አንድ ሰው ከእነሱ ጋር እንዲኖር ይፈልጋሉ ወይንስ በዙሪያው መከታተል የማይገባቸው ሰዎች አሉ? ለዘጋቢ ፊልም ሰሪዎች፣ ሰራተኞቹን መቀነስ ያስቡበት።
- ምስሎቹ ከተነሱ በኋላ ስለተነሱበት መንገድ ደስተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለተጎጂዎቹን ለማሳየት ያስቡበት።
- የተጎጂዎች ምስሎቻቸው ለረጅም ጊዜ ሊኖሩ እንደሚችሉ እና በመድረኮች ላይ፣ በራሳቸው ማህበረሰብ ውስጥም ቢሆን መጋራት እንደሚችሉ መረዳታቸውን ያረጋግጡ።

ሥራውን በፍጥነት ለመጨረስ የማትቸኩልባቸው መንገዶች አሉ? የምስሎች ቀረጻ እንዴት እንደሚሆን አስቀድመው መወያየት እና ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ማብራራት ይችላሉ? በአንድ ጎልማሳ ሰው በኩል እንኳን ቢሆን፡ ልጆች ማንነታቸው እንዲጋራ በፍጹም ፈቃድ መስጠት እንደማይችሉ ያስታውሱ።

### የፎቶ ጋዜጠኝነት እና አዘጋጆች

> አንድ ፎቶግራፍ አንሺ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በጭንቅላታቸው ላይ እንደማይሆኑ ሊረዳ እችላለሁ፣ አዘጋጅ እንደዛ ሲሆን ግን አስደንጋጭ ነው።
>
> ለአዘጋጆች፣ ከታሪካዊ ሁኔታዎች አንፃር የምስል እውቀት ያለው መሆን በተመለከተ የበለጠ የኃላፊነት ስሜት እንዳለ ይሰማኛል።
>
> ኒና በርማን [ሀ]

---

ሀ. ኒና በርማን በቦዝኒያ እና አፍጋኒስታን ግጭቶችን የዘገበች የዘጋቢ ሰዕል አንሺ ነች። ለዚህ ፕሮጀክት በተደረገ ምርምር አስተዋፅዖ ያበረከተች ስትሆን፡ በግጭት እና በሰላማዊ ጊዜ የፎቶግራፍ ሥነ-ምግባር ላይ የጻፈች እና በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት ፕሮፌሰር ነች። ለተጨማሪ፡ እዚህ ይመልከቱ፡ https://dartcenter.org/resources/visual-choices-covering-sexual-violence-conflict-zonesconflict-zones

ፎቶግራፍ አንሺዎች ከተጎጂዎች ጋር ስለሚገናኙ ስለ ምስላዊ ምርጫዎች ውሳኔ ያደርጋሉ። ነገር ግን አዘጋጆች የትኞቹ ምስሎች መነሳት እንዳለባቸው ይሁን ለህዝብ ከመድረሳቸው በፊት ከተሰበሰቡት ምስሎች የትኞቹ እንደሚመረጡ የመጨረሻ ኃላፊነት አለባቸው። ለውስጣዊ ገጽ ተገቢ ሊሆን የሚችለው – ትርጉም እና ነባራዊ ሁኔታን የሚያካትት – በሽፋን ላይ ወይም በኢንስታግራም ልጥፍ ላይ ብቻውን የሚቆም ሲነጻጸር ሙሉ በሙሉ የተለየ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል።

አዘጋጆች፣ ከባለሙያዎች በሚገኝ ድጋፍና እና ከሜዳው ጫና ርቆ ስልታዊ በሆነ መንገድ ለማሰብ በሚረዳ ጊዜ ተደግፈው፣ ፎቶግራፍ ሆን ተብሎ ወይም ባለማወቅ የሚጠቅሰውን ምስላዊ ቋንቋ ማጤን አለባቸው። በባርነት ስለየተያዙ ሰዎች የረዥም ጊዜ ታሪክ አለ፣ ለምሳሌ፣ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ የሚሰሩ ምስል ሰሪዎች ሊያስወግዱት የሚገባ።

የፎቶ አርታኢዎች ምስልን በሚመለከት ጥቅም ከዋለበት በኋላ ስለሚኖረው ዕድሜ ሳይቀር የመወሰን ስልጣን አላቸው – ፍቃድ አሰጣጥ እና ተደራሽነት – እንዲሁም በማህበራዊ አውታረ መረቦች ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት መንገድ።

እንደ አርታኢ፣ ከረጅም ጊዜ የስራ ባልደረቦችዎ ጋር እየሰሩ ወይም በጭራሽ ያላገኟቸው ነፃ ጋዜጠኞችን በማስማራት ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለ ድንበሮች፣ ትርጉም ያለው ስምምነት እና ማንነትን ስለመደበቅ ለአጭር የ10 ደቂቃ ውይይት ጊዜ መስጠት ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። ሊታሰብባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች እነዚህ ናቸው፦

- በስምምነት ዙሪያ ከፎቶግራፍ አንሺዎች ጋር ትክክለኛ ውይይት አድርገዋል? [**ቁ.3** ይመልከቱ]
- ተጎጂዎች እንዲታወቁ አስፈላጊነት አለው? ማንነታቸው እንዳይገለጽ በሚያደርጉበት ጊዜ ምን ዓይነት የእይታ ጥገናዎች ይሰራሉ?
- መግለጫ ጽሑፎች የታሪኩ አካል ስለሆኑ፡ ልክ እንደ ምስሎቹ፣ ሰውየውን ወሲባዊ ማድረግ ወይም ማዋረድ የለባቸውም። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ሰለባ የሆኑ ሰዎችን ምስሎችን የጊዜ ገደብ መስጠት ይችላሉ?
- ለዜና ተቋማት ላይ የማይሸጡ ለአንድ ዘገባ ጥቅም ብቻ የሚውሉ ሊያደርጓቸው ይችላሉ? በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ምስሎችን እንዴት እየተጠቀሙባቸው ነው?
- ለምሳሌ በኢንስታግራም ላይ የተጎጂው ፊት ወይም አካል ማሳየት አለብዎት ወይስ አንድ ግለሰብ ሙሉውን ክብደት እንዲሸከም በማያደርግ መልኩ ታሪኩን የሚያስተዋውቁበት ሌላ መንገድ አለ?

ይህንን
ጽሑፍ ያጋሩ